# Table of Contents


| | |
|---|---|
| PART ONE: GENERAL | 6 |
| 1. Short Title | 6 |
| 2. Definition | 6 |
| 3. Scope of Application | 7 |
| PART TWO: PUBLIC EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE | 7 |
| SECTION ONE: EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE | 7 |
| 4. Recruitment and Placement of Worker | 7 |
| 5. Types of Services | 8 |
| 6. Prohibition of Direct Employment | 8 |
| SECTION TWO: EDUCATION, TRAINING AND MEDICAL EXAMINATION | 9 |
| 7. Educational level and Occupational Competence Assessment | 9 |
| 8. Awareness Raising Program | 9 |
| 9. Medical Examination | 10 |
| SECTION THREE: EXPENSE COVERAGE AND SERVICE FEE | 10 |
| 10. Expense Coverage | 10 |
| 11. Service Fee | 11 |
| SECTION FOUR: BILATERAL AGREEMENT AND STRUCTURE | 11 |
| 12. Requirement of Bilateral Agreement | 11 |
| 13. Structure | 11 |
| 14. Assignment of a Labour Attaché | 12 |
| 15. National Coordinating Committee and Task Force | 12 |
| PART THREE: CONDITIONS OF WORK | 13 |
| SECTION ONE: DETERMINATION OF CONDITIONS OFWORK | 13 |
| 16. Working Condition | 13 |
| 17. Content of Model Contract of Employment | 13 |
| 18. Freedom of Parties to Stipulate Contract | 14 |
| 19. Obligation to Disclose | 14 |
| SECTION TWO: INSPECTION SERVICE | 14 |
| 20. Inspection | 14 |
| PART FOUR: OVERSEAS EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE THROUGH AN AGENCY | 16 |
| SECTION ONE: LICENSE, ELIGIBILITY AND NONELIGIBILITY FOR LICENSE | 16 |

| | |
|---|---|
| 21. Requirement of a License | 16 |
| 22. Eligibility to Obtain License | 16 |
| 23. Non-eligibility to Obtain License | 17 |
| SECTION TWO: ISSUANCE OF LICENSE | 17 |
| 24. Requirements to Obtain License | 17 |
| 25. Issuance of License | 19 |
| 26. Validity of License | 19 |
| 27. Display of License in Conspicuous Place | 19 |
| 28. Non-transferability of License and Prohibition of Engagement in more than one Agency | 20 |
| 29. Notification of Change of Management or an Employee | 20 |
| 30. Making Management Personnel Public | 20 |
| 31. Opening Additional Local Offices | 20 |
| 32. Change of Business Address and Notification | 21 |
| 33. Renewal of License | 21 |
| 34. Incentive Scheme | 22 |
| SECTION THREE: EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE | 22 |
| 35. Advertisement for Overseas Employment | 22 |
| 36. Recruitment of Worker | 23 |
| 37. Approval of Contract of Employment | 23 |
| 38. Deployment of Worker and Reporting | 23 |
| 39. Revocation of Contract of Employment | 24 |
| 40. Joint and Several Liability | 24 |
| PART FIVE: VIOLATION AND CORRESPONDING MEASURE | 24 |
| SECTION ONE: VIOLATIONS BY AN AGENCY AND CORRESPONDING CORRECTIVE MEASURES | 24 |
| 41. Power to Decide Administrative Matters | 24 |
| 42. Type of Contraventions | 24 |
| 43. Submission of Complaint | 27 |
| 44. Content of Complaint | 28 |
| 45. Complaint Hearing | 28 |
| 46. Temporary Measure | 29 |
| 47. Administrative Measure | 29 |
| 48. Legal consequences of license suspension or Revocation | 30 |

49. Content of Decision 30
50. Execution Order 31
51. Priority of Execution 31
SECTION TWO: VIOLATIONS BY AN EMPLOYER, AN AGENCY'S REPRESENTATIVE AND WORKERS AND THE CORRESPONDING MEASURES 31
52. Power to Decide Administrative Matters 31
53. Violations Committed by Employer and Representative of Agency 32
54. Complaint Against an Employer or a Representative Agency and the Decision Making 32
55. Content of the Complaint 33
56. Legal Consequence of the Decision 33
57. Contraventions by a worker 33
58. Administrative Measures 34
59. Right to Lodge Pleading before Court of Law 34
PART SIX: WELFARE SERVICE 34
SECTION ONE: FINANCIAL GUARANTEE AND INSURANE 34
60. Financial Guarantee 34
61. Foreign Employers' Guarantee Fund 35
62. Insurance Coverage 36
SECTION TWO: ASSISTANCE PROVIDED TO WORKERS 36
63. Responsibility 36
64. Provision of Support 36
65. Registration of worker on leave or Vacation 37
SECTION THREE: CONCILIATION AND REPATRIATION OF WORKERS 37
66. Conciliation 37
67. Conciliation Proceedings 37
68. Administrative Measures 38
69. Repatriation of Workers 38
PART SEVEN: MISCELLANEOUS PROVISIONS 38
70. Determining Number of Agencies Work with one Representative and an Agency with Representatives 38
71. Labor Dispute Resolution 39
72. Burden of Proof 39
73. Period of Limitation 39
74. Prohibition 39

| | | |
|---|---|---|
| 75. | Power to issue Regulation and Directives | 39 |
| 76. | Duty to Cooperate | 40 |
| 77. | Repeal and Inapplicable Laws | 40 |
| 78. | Transitory Provisions | 40 |
| 79. | Effective Date | 41 |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ የካቲት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.44
ADDIS ABABA 19th February , 2016

አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ……………………………………………………..…..ገጽ ፰ሺ፰፻፷፩

Proclamation No. 923/2016

Ethiopia's Overseas Employment Proclamation ………………………………………Page 8861

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰

## የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት የወጣ አዋጅ

መሥራት ለሚችሉ ዜጎች ሁሉ በአገር ውስጥ ምቹ የሥራ ዕድሎች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ለመፍጠር መንግሥት የሚያደርገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ውጭ አገር በመሄድ ለመሥራት ፍላጎት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን መብታቸው፣ ደህንነታቸው እና ክብራቸው ተጠብቆ ባላቸው ችሎታና አቅም ሠርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከተቀባይ አገሮች ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት መፈራረም ሕጋዊ የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን በማጠናከር ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል ጠቃሚ መሆኑ በመታመኑ፤

የግሉ ዘርፍ በውጭ አገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት አሰጣጥ ሊኖረው የሚገባውን ተሳትፎ በሕግ መወሰን በማስፈለጉ፤

መንግሥት በውጭ አገር ሥራ ስምሪት አፈጻጸም የሚኖረውን የክትትልና የቁጥጥር ሚና ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሥራ ላይ የነበረውን የሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ በአዲስ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ሕግ መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## Proclamation No. 923/2016

## ETHIOPIA'S OVERSEAS EMPLOYMENT PROCLAMATION

WHEREAS, the Government's commitment to create a favorable domestic condition for promoting employment opportunities for those who are able to work is intact, it has been found necessary to protect the rights, safety and dignity of Ethiopians who are willing to take-up overseas employment in pursuance of their qualifications and ability;

WHEREAS, it is believed that bilateral agreements with receiving countries may strengthen lawful overseas employment and could prevent human trafficking;

WHEREAS, it has become necessary to define the role of the private sector in overseas employment exchange services;

WHEREAS, it has become essential to enhance the role of the Government in the follow-up and monitoring of overseas employment exchange services;

WHEREAS, it has become necessary to replace existing Employment Exchange Services Proclamation with new Overseas Employment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is



https://ethiodata.et/

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት አዋጅ ቁጥር ፱፻፳፫/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፦

፩/ "የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ" ወይም "ኤጀንሲ" ማለት መንግሥታዊ አካል ያልሆነና ከሠራተኛ ጋር የሥራ ውል ስምምነት በማድረግ ሠራተኛን በውጭ አገር ለሥራ ለአሠሪ የማቅረብ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤

፪/ "ፈቃድ" ማለት በሚኒስቴሩ ለኤጀንሲ የሚሰጥ በግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፤

፫/ "አሠሪ" ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ በተመለከተው የሥራ ውል መሠረት በኤጀንሲ አማካኝነት፣ መንግሥት-ለመንግሥት በሚደረግ ስምምነት ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በቀጥታ ቅጥር የሚያሰራ ሰው ነው፤

፬/ "ሠራተኛ" ማለት በዚህ አዋጅ በተመለከተው የሥራ ውል መሠረት ከአሠሪ ወይም ከኤጀንሲ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ሲሆን፣ እንደአግባቡ ሥራ ፈላጊንም ይጨምራል፤

፭/ "ቀጥታ ቅጥር" ማለት የመንግሥታዊ አካል ወይም የኤጀንሲ አገልግሎት ሳይሰጥ አሠሪውና ሠራተኛ በራሳቸው በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈፀም ቅጥር ነው፤

፮/ "የሥራ ሁኔታ" እና "የሥራ ላይ አደጋ" ማለት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተሰጣቸውን ትርጉም ይኖራቸዋል፤

፯/ "የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ" ማለት አንድ ሠራተኛ ለሚቀጠርበት ሥራ የመሥራት ብቃት ያለው ስለመሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ተመዝኖ የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopia's Overseas Employment Proclamation No. 923/2016".

**2. Definition**

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "Private Employment Agency" or "Agency" means any person other than a Government body, which makes a worker available to an overseas employer by concluding a contract of employment with such a worker;

2/ "license" means a certificate of competence issued by the Ministry to an Agency enabling the latter to engage in providing overseas employment exchange services;

3/ "employer" means any person who employs one or more persons through an Agency or through Government to Government arrangement or through direct employment in accordance with this Proclamation;

4/ "worker" means an individual who has a contractual relation with an employer or an Agency in accordance with this Proclamation and it may, as the case may be, include a job-seeker;

5/ "direct employment" means an employ ment relationship between an employer and a worker without the involvement of a Government organ or an Agency;

6/ "condition of work" and "occupational accident" shall have the meanings provided for under Labour Proclamation;

7/ "certificate of occupational competence" means a document issued by an authorized organ evidencing that the worker is capable of performing a particular task;

8/ "family" means a spouse, ascendants, descendants or relatives up to a second

፰/ "ቤተሰብ" ማለት የትዳር ጓደኛ፣ ወላጅ፣ ተወላጅ ወይም እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ የሚቆጠር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ነው፤

፱/ "የሁለትዮሽ ስምምነት" ማለት የውጭ አገር የሥራ ቅጥር አስመልክቶ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በተቀባይ አገር መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው፤

፲/ "ሚኒስቴር" ማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤

፲፩/ "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት በክልል የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎችን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፫/ "ሚሲዮን" ማለት በውጭ ሀገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣ ቋሚ መልእክተኛ ጽሕፈት ቤት፣ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም የንግድ ጽሕፈት ቤት ነው፤

፲፬/ "ንግድ ማህበር" ማለት የሽርክና ማህበር፣ የአክሲዮን ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው፤

፲፭/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮/ በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም አገላለፅ ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ ፦

፩/ በመንግሥታዊ አካል፣ በኤጀንሲ አማካኝነት ወይም በቀጥታ በሚደረግ ቅጥር የኢትዮጵያዊያን የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ግንኙነት ላይ፣

፪/ ለትርፍ በሚካሄድ ሥራ ላይ ላልተመሠረተ ለቤት ሠራተኛነት ለመቀጠር ወደ ውጭ አገር በሚሄድ ኢትዮጵያዊ ላይ፣

ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## በመንግሥት ስለሚሰጥ የሥራ ስምሪት አገልግሎት

## ንዑስ ክፍል አንድ

degree through consanguinity or affinity;

9/ "bilateral agreement" means an agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the receiving country pertaining to overseas employment;

10/ "Ministry" means the Ministry of Labour and Social Affairs

11/ "appropriate authority" means a Regional Government organ entrusted with the power to implement labour laws;

12/ "region" means any Regional State specified under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

13/ "mission" means Ethiopia's diplomatic mission, permanent mission, consular office or trade office abroad;

14/ "business organization" means a partnership, share company or private limited company;

15/ "person" means any natural or juridical person;

16/ any expression to the masculine gender includes the feminine.

3. **Scope of Application**

This Proclamation shall apply to:

1/ overseas employment relation of Ethiopians' conducted by public employ ment organs, through Agency or on direct employment;

2/ Ethiopians travelling to abroad to engage in overseas contracts of house maid service for non-profit making purposes.

## PART TWO

## PUBLIC EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE

## SECTION ONE

## EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE

4. **Recruitment and Placement of Worker**

https://ethiodata.et/

## ስለሥራ ስምሪት አገልግሎት

### ፬. የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎት



ሚኒስቴሩ መንግሥት ለመንግሥት በሚደረግ ስምምነት መሠረት በተቀባይ አገር ለሚገኝ መንግሥታዊ ድርጅት የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎቶችን ሊሰጥ ይችላል፡፡

### ፭. ስለአገልግሎት ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት በሚኒስቴሩ የሚሰጡ የሠራተኛ ምልመላና ስምሪት አገልግሎቶች ቃለ መጠይቅና መረጣ ማድረግን፣ የጤና ምርመራ እንዲከናወን ማድረግን፣ የሥራ ውል ማፅደቅን፣ የቅድመ-ቅጥር እና ቅድመ-ጉዞ ገለፃ መስጠትን፣ የተቀጣሪ ሠራተኛ የውጭ ጉዞ ማመቻቸትን እና የመሳሰሉትን ሌሎች አገልግሎቶች ይጨምራል፡፡

### ፮. ቀጥታ ቅጥር የተከለከለ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም አሠሪ በሚኒስቴሩ ወይም በኤጀንሲ በኩል ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ ሠራተኛን መልምሎ ሊቀጥር አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሚኒስቴሩ በሚከተሉት ሁኔታዎች ቀጥታ ቅጥር ሊፈቅድ ይችላል፦

ሀ) አሠሪው የኢትዮጵያ ሚሲዮን አባል ከሆነ፤

ለ) አሠሪው ዓለም አቀፍ ድርጅት ከሆነ፤ ወይም

ሐ) ከየቤት ሰራተኛነት ቅጥር በስተቀር ማንኛውም ሥራ ፈላጊ በራሱ ጥረት የሥራ ዕድል ሲያገኝ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) መሠረት በቀጥታ የሚደረግ ቅጥር በሚኒስቴሩ ሊፈቀድ የሚችለው ፦

ሀ) ሠራተኛው በሚሄድበት አገር መብቱ፣ ደህንነቱና ክብሩ ሊጠበቅ እንደሚችል በሚመለከተው ሚሲዮን ወይም በተቀባዩ አገር ሚሲዮን ከሌለ አዲስ አበባ በሚገኘው የተቀባዩ አገር ሚሲዮን እና በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ፣

The Ministry may provide recruitment and placement services to Governmental organization in receiving country based on Government to Government agreement.

### 5. Types of Services

The services to be provided by the Ministry pursuant to Article 4 of this Proclamation shall include interviewing and selection; causing medical examinations; approval of employment contracts, provision of pre-employment and pre-departure orientations, facilitation of departure of employed workers and other similar services.

### 6. Prohibition of Direct Employment

1/ No employer shall directly recruit and employ a worker except through the Ministry or an Agency.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, the Ministry may permit direct employment on the following grounds:

a) where the employer is a staff of an Ethiopian Mission;

b) where the employer is an International organization; or

c) where the job seeker acquires a job opportunity by his own accord in job positions other than house maid service.

3/ The direct employment pursuant to paragraph (c) of sub-article (2) of this Article may be permitted by the Ministry only when evidence of the following are secured:

a) an assurance secured from a pertinent mission or from mission of country of destination if an Ethiopian mission is not present in the country of destination; and the Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia that the worker's basic rights and dignity will be respected in the country of destination;

b) life and disability insurance coverage for the worker pursuant to Article 62(1) of this Proclamation has been issued;

c) appropriate air or land transport service together with contract of employment are submitted.

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ (፩) መሠረት የተገባ የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሣ ኢንሹራንስ ሽፋን ስለመኖሩ፣ እና

ሐ) ከሥራ ውሉ ጋር ምቹ የሆነ የአየር ወይም የየብስ መጓጓዣ አገልግሎት የሚያገኝ ስለመሆኑ፣

ማስረጃ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ቀጥታ ቅጥር እንዲፈፅም ለተፈቀደ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ሊወጣ የሚችለው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን በኩል ብቻ ነው፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ትምህርት፣ ሥልጠና እና የጤና ምርመራ

### ፯. ስለ ትምህርት ደረጃና የሙያ ብቃት ምዘና

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ማንኛውም ሠራተኛ ፦

ሀ) ቢያንስ የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ፣ እና

ለ) በሚቀጠርበት የሥራ መስክ አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የያዘ፣

መሆን አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሠራተኛው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚጠየቀው አሠሪው የሚጠይቃ ቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

### ፰. ስለ ግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራም

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ፦

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ስለተቀባይ አገር ሁኔታ፣ በሚሰማሩበት የሥራ መስክ ሊኖራቸው ስለሚገባ ክህሎት፣ ስለመብታቸውና ኃላፊነታቸው እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች የቅድመ-ስምሪትና የቅድመ-ጉዞ ግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና በመደበኛነት ይሰጣል፣

4/ An advertisement to vacant positions permitted for direct employment pursuant to this Article shall only be conducted through the Ministry or the appropriate authority.

## SECTION TWO
## EDUCATION, TRAINING AND MEDICAL EXAMINATION

### 7. Educational level and Occupational Competence Assessment

1/ Any worker who desires to take-up overseas employment shall:

a) at least complete eighth grade education;

b) possess a certificate of occupational competence issued by the appropriate competence assessment center for the work he is to be employed.

2/ The worker shall be required to present certificate of occupational competence pursuant to sub-article (1) of this Article only when the fulfillment of other requirements set by the employer are ascertained.

### 8. Awareness Raising Program

The Ministry or the appropriate authority shall:

1/ undertake regular pre-employment and pre-departure awareness raising to citizens who show interest to take-up overseas employment pertaining to the conditions of receiving countries, the required skill for a job position they are taking, their rights and duties and similar other matters;

2/ conduct continuous national awareness raising activities to the public at large by using mass media and disseminating correct and up-to-date information regarding overseas employment.

3/ conduct regular awareness raising programs to Agencies' board of directors, general managers and employees on issues related to overseas employment;

https://ethiodata.et/

፪/ ሕብረተሰቡ ስለውጭ አገር ሥራ ስምሪት ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኝ የመገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም ቀጣይነት ያለው አገር አቀፍ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፫/ ለኤጀንሲ የቦርድ አመራሮች፣ ሥራ አሥኪያጆች እና ሠራተኞች ስለውጭ አገር ሥራ ስምሪት ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማሳደጊያ ፕሮግራ ሞችን ያካሂዳል፤

፳ሺ፳፻፳፮

፬/ ስለ ኢትዮጵያዊያን ሠራተኞች ምልመላና ቅጥር ሁኔታ፣ ስለውጭ አገር ሥራ ስምሪት በሥራ ላይ ስላሉ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ቅድመ ሁኔታዎች እና የተለያዩ መስፈርቶች ለውጭ አገር አሠሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ይሰጣል፡፡

## ፱. ስለ ጤና ምርመራ

፩/ የሠራተኛ የጤና ምርመራ የሚደረገው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚመርጠው የጤና ተቋም ብቻ ይሆናል፡፡

፪/ ኤጀንሲው ሠራተኛን ለጤና ምርመራ መላክ ያለበት አሠሪው የሚጠይቃቸውን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላቱ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ ሠራተኛው ከአንድ ጊዜ በላይ የጤና ምርመራ እንዲያደርግ የሚጠየቅ ከሆነ ወጪውን ኤጀንሲው መሸፈን ይኖርበታል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለወጪ አሸፋፈንና የአገልግሎት ክፍያ

## ፲. ስለ ወጪ አሸፋፈን

፩/ የሚከተሉት ወጪዎች በአሠሪው ይሸፈናሉ፦

ሀ) የተቀባይ አገር የመግቢያ ቪዛ ክፍያ፤

ለ) የደርሶ መልስ የመጓጓዣ ክፍያ፤

ሐ) የሥራ ፈቃድ ክፍያ፤

መ/ የመኖሪያ ፈቃድ ክፍያ፤

ሠ) የመድህን ዋስትና ሽፋን፤

ረ) በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኝ ለተቀባይ አገር

4/ carryout awareness creation orientation to foreign employers on the conditions of recruitment and employment of Ethiopian employees, existing laws, regulations, directives, requirements and standards for overseas employment.

## 9. Medical Examination

1/ The medical examination of a worker shall only be undertaken in a medical institution selected by the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health.

2/ The Agency shall refer the worker for medical examination only when it is ascertained that the worker fulfills other requirements of the Employer.

3/ Whenever a worker is required to undergo a medical examination more than once, such expense shall be covered by the Agency.

## SECTION THREE

## EXPENSE COVERAGE AND SERVICE FEE

## 10. Expense Coverage

1/ The employer shall cover the following expenses:

a) entry visa fee to the country of destination;

b) round-trip transport cost;

c) work permit fee;

d) residence permit fee;

e) insurance coverage;

f) costs associated with visa and document authentication paid to the embassy of country of destination which hosts in Ethiopia;

g) employment contract approval service fee.

2/ The worker shall cover the following expenses:

a) passport issuance fee;

b) costs associated with authentication of contract of employment received from overseas and certificate of

https://ethiodata.et/

ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት የሚከፈል ከቪዛና ከሰነድ ማረጋገጥ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ወጪ፣ እና

ሰ) የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ክፍያ፡፡

፪/ የሚከተሉት ወጪዎች በሠራተኛው ይሸፈናሉ፡-

ሀ) የፓስፖርት ማውጫ ወጪ፣

ለ) ከውጭ አገር የሚላክ የሥራ ቅጥር ውል ሰነድ እና ከወንጀል ነፃ ማስረጃ ማረጋገጫ ወጪ፣



ሐ) የሕክምና ምርመራ ወጪ፣

መ) የክትባት ወጪ፣

ሠ) የልደት ሰርተፊኬት ማውጫ ወጪ፣ እና

ረ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ወጪ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱ ወጪዎችን ሠራተኛው አውጥቶ በራሱ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት በሥራ ላይ ካልተሰማራ ኤጀንሲው ወይም አሰሪው የሠራተኛውን ወጪ የመተካት ግዴታ ይኖርበታል፡፡

፬/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ አስፈላጊ ሁኔታዎች ተጠናቀው ያለበቂ ምክንያት ሠራተኛው ወደ ሥራው ባይሰማራ ከቅጥሩ ጋር በተያያዘ አሰሪው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ያወጣውን ወጪ ሠራተኛው እንዲከፍለው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ፲፩. ስለ አገልግሎት ክፍያ

ሚኒስቴሩ አሠሪውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሥራ ውል ማፅደቂያ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ ያስከፍላል፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት
## ስለሁለትዮሽ ስምምነት እና አደረጃጀት

## ፲፪. የሁለትዮሽ ስምምነት ስለማስፈለጉ

በዚህ አዋጅ መሠረት ሠራተኛን በውጭ አገር ለሥራ ማሰማራት የሚቻለው በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በተቀባይ አገር መካከል የሁለትዮሽ ስምምነት ሲኖር ብቻ

clearance from crime;

c) medical examination fee;

d) vaccination fee;

e) birth certificate issuance fee;

f) expenses for certificate of occupational competence.

3/ The Agency or employer shall refund the worker's expenses referred to in sub-article (2) of this Article, if the worker fails to be deployed for work for reasons not attributable to him after incurring the expense.

4/ Whenever the worker, without justified cause, fails to be deployed for work after all requirements for departure are fulfilled, the employer may require the worker to refund expenses incurred regarding the employment pursuant to sub-article(1) of this Article.

## 11. Service Fee

The Ministry shall charge the employer a service fee associated with the approval of contract of employment in accordance with Regulations issued by the Council of Ministers.

## SECTION FOUR
## BILATERAL AGREEMENT AND STRUCTURE

## 12. Requirement of Bilateral Agreement

Deployment of workers for overseas employ ment in accordance with this Proclamation shall be effected only if there is a bilateral agreement concluded between the Federal Democratic Republic of Ethiopian and the receiving country.

## 13. Structure

1/ The Ministry shall establish the necessary organizational structure in order to discharge the responsibilities entrusted to it by this Proclamation.

2/ The appropriate authority shall, at a regional level, establish the necessary organizational structure in order to discharge the responsibilities entrusted to it by this Proclamation.

https://ethiodata.et/

ነው፡፡

**፲፫. ስለአደረጃጀት**

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባሮች ለማከናወን አስፈላጊውን አደረጃጀት ይፈጥራል::

፪/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባሮች በክልል ደረጃ ለማከናወን አስፈላጊውን አደረጃጀት ይፈጥራል፡፡



**፲፬. ሌበር አታሼ ስለመመደብ**

፩/ ሚኒስቴሩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመመካከርና መንግሥትን በማስፈቀድ በውጭ አገር ለሥራ የሚሰማሩ ዜጎች መብት፣ ደህንነት እና ክብር እንዲጠበቅ ሌበር አታሼ በተቀባይ አገር በሚገኘው ሚሲዮን እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመደበው የሌበር አታሼ ተግባርና ኃላፊነት ሚኒስቴሩ እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጋራ በሚያወጡት የአሰራር መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲፭. ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ግብረ ኃይል**

፩/ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፱/፪ሺ፯ አንቀፅ ፴፱ መሰረት የተቋቋመው ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ ላይ የተመለከቱትን ተግባራት ይፈፅማል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት ለብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴው ተጠሪ የሆነው ግብረ ኃይል የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

**14. Assignment of a Labour Attaché**

1/ The Ministry shall, in consultation with the Ministry of Foreign Affairs, and after obtaining permission from Government, cause the assignment of a Labour Attaché in the mission of the receiving country to ensure protection of the rights, safety and dignity of workers employed overseas.

2/ The duties and responsibilities of the labour attaché to be assigned pursuant to sub-article (1) of this Article shall be determined by a rule of operation to be issued jointly by the Ministry and the Ministry of Foreign Affairs.

**15. National Coordinating Committee and Task Force**

1/ The National Coordinating Committee established by Article 39 of the proclamation No. 909/2015 issued to provide for the prevention and suppression of human trafficking and smuggling of migrants shall perform the activities listed under sub article 2.

2/ the task force accountable to the National coordinating Committee established by the proclamation stated under sub article 1 of this article shall have the following powers and duties to:

a) ensure the proper implementation of this Proclamation;

b) ensure proper provision of cooperation and support relevant to the objectives of organs engaged in counseling and reintegration activities of returnees;

c) cause the conduct of studies with a view to concluding bilateral agree ments with receiving countries on issues related to employment and thereby establish conducive situation;

d) cooperate with appropriate organs and ensure the taking legal action against those responsible for violation of rights or damage inflicted on citizens in the receiving countries;

ሀ/ ይህ አዋጅ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

ለ/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር ሄደው በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አገራቸው ለሚመለሱ ዜጎች የምክር አገልግሎት የሚሰጡና የመልሶ ማቋቋም ፕሮግራሞችን የሚያካሂዱ አካላት አስፈላጊውን ትብብርና ድጋፍ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ/ ከሥራ ስምሪት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ከተቀባይ አገራት ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት ሊደረግ ስለሚችልበት ሁኔታ እንዲጠናና አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

መ/ በተቀባዩ አገር ውስጥ በዜጎች ላይ የመብት መጣስ ወይም ጉዳት ሲደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለዚሁ ተጠያቂ በሆኑ ሰዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤



ሠ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሕገወጥ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ድርጊት የሚሳተፉ ሰዎች በአፋጣኝ ሕግ ፊት ቀርበው መዳኘታቸውን ያረጋግጣል፤

ረ/ ሕገወጥ ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት ድርጊትን በተመለከተ ለሕብረተሰቡ የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤

ሰ/ የውጭ አገር ሥራ ስምሪትን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ እንዲደረግና የተጠናከረ የመረጃ ማዕከል እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሸ/ የራሱን የአሰራር መመሪያ ያወጣል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ስለ ሥራ ሁኔታዎች**

**ንዑስ ክፍል አንድ**

**የሥራ ሁኔታዎችን ስለመወሰን**

**፲፮. ስለ ሥራ ሁኔታ**

ሚኒስቴሩ ወቅታዊ የውጭ አገር የሥራ ገበያ ሁኔታዎችን እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን አስመልክቶ የሥራ ሁኔታ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፯. ስለ ሞዴል የሥራ ውል ይዘት**

e) ensure, in cooperation with concerned authorities, that persons involved in human trafficking are immediately brought before justice;

f) cause the provision of awareness creation training to public on illegal employment exchange activities;

g) facilitate the exchange of overseas employment information with concerned organs and the establish ment of well-equipped data center;

h) adopt its own rules of operations.

**PART THREE**

**CONDITIONS OF WORK**

**SECTION ONE**

**DETERMINATION OF CONDITIONS OF WORK**

**16. Working Condition**

The Ministry may issue directive on working condition regarding prevailing overseas labour market and social services.

**17. Content of Model Contract of Employment**

1/ The Ministry shall prepare model contract of employment, at least including the following:

a) regular working time,favorable wages for regular working hours and overtime pay, as appropriate, which shall not be lower than the prescribed minimum wage in the receiving country, the appropriate minimum wage set by the bilateral agreement, international agreements ratified by both countries, whichever is highest;

b) annual leave, weekly rest and other similar vacations;

c) free transportation to and from the worksite or offsetting benefit;

d) free medication, food and accommo dation or offsetting benefits;

e) insurance coverage for life or disability;

፩/ ሚኒስቴሩ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ ሞዴል የሥራ ውል ያዘጋጃል፡-

ሀ) በተቀባይ አገር መነሻ ክፍያ ተብሎ ከተወሰነው፣ ኢትዮጵያና ተቀባይ አገር ባደረጉት የሠራተኛ ቅጥር ሁለትዮሽ ስምምነት መነሻ ክፍያ ተብሎ ከተደረሰው፣ ሁለቱ አገሮች ባፀደቁት ዓለም አቀፍ ስምምነት ከተመለከተው አነስተኛ የደመወዝ መጠን የማያንስ እና የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ የደመወዝ፣መደበኛ የሥራ ሰዓት እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

ለ) የዓመት፣ የሣምንት እና የመሳሰሉት ዕረፍቶች፣

ሐ) ወደ ሥራ ቦታ መሄጃና ከሥራ ቦታ መመለሻ ነፃ የትራንስፖርት አገልግሎት ወይም ተመጣጣኝ ክፍያ፣

መ) ነፃ ሕክምና፣ ምግብና መጠለያ ወይም ተመጣጣኝ ክፍያ፣

ሠ) የሕይወትና የአካል ጉዳት ዋስትና ሽፋን፣

ረ) የሥራ ውል የሚቋረጥባቸው በቂ ምክንያቶች ፡፡

፰ሺ፰፻፸

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሞዴል የሥራ ውል ሲዘጋጅ በመሠረታዊነት የሚከተሉት መገናዘብ ይኖርባቸል፡-

ሀ) የተቀባይ አገር ባህል፣ ልማድ፣ አኗኗር፣ የሠራተኛ እና የማህበራዊ ጉዳይ ሕጎች እንዲሁም የአሠሪ ድርጅት ፖሊሲዎች፣

ለ) ከተቀባይ አገር ጋር የተፈረሙ አግባብ ያላቸው የሁለትዮሽ እና የብዙ ወገን ስምምነቶች፣ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች እና ውሳኔዎች፣

ሐ) የሥራ ገበያው ወቅታዊ ሁኔታዎች፡፡

**፲፰. <u>የተዋዋይ ወገኖች ነፃነት</u>**

ለሠራተኛ ይበልጥ የሚጠቅም እና የኢትዮጵያ የመንግሥት ፖሊሲ፣ ሕግንና የሕብረተሰቡን ሞራል የማይቃረን እስከሆነ ድረስ ተዋዋይ ወገኖች በሞዴል የሥራ ውል ያልተመለከቱ ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችንና ጥቅሞችን በሥራ ውላቸው ውስጥ ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

f) valid grounds for termination of contract of employment.

2/ When model contract of employment is to be formulated as provided under sub-article (1) of this Article, basically, the following shall be taken into account:

a) the culture, custom, way of life and the labour and social affairs laws of the receiving country and the policies of the employing enterprise;

b) relevant bilateral and multilateral treaties signed with receiving country, international conventions and resolutions;

c) prevailing labor market conditions.

**18. <u>Freedom of Parties to Stipulate Contract</u>**

Parties to overseas employment contract are at liberty, without contravening Ethiopian government policies, laws and public morality, to stipulate other terms, conditions and benefits that are not provided for in the model contract if it is more beneficial to the worker than the minimum set in the model contract.

**19. <u>Obligation to Disclose</u>**

1/ Any Agency shall, to the Ministry, appropriate authority or the mission, disclose within appropriate time all relevant information related to recruitment and placement of workers and other information may be requested with respect to condition of worker.

2/ The Ministry shall issue directive to determine the appropriate time for provision of information pursuant to sub-article (1) of this Article.

## <u>SECTION TWO</u>
## <u>INSPECTION SERVICE</u>

**20. <u>Inspection</u>**

1/ The Ministry shall, in order to ensure the legality of workers going for overseas employment, issue special identification cards for those whose contract of employment has been approved.

2/ The Ministry or the appropriate authority shall assign labour inspector to monitor

## ፲፱. የማሳወቅ ግዴታ

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ ከሠራተኛ ምልመላና ቅጥር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች እና ስለሠራተኛው ሁኔታ የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ሁሉ ለሚኒስቴሩ፣ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ወይም ለሚሲዮኑ ተገቢ በሆነ ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት መረጃዎች ሊቀርቡበት የሚገባውን ጊዜ ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ስለ ቁጥጥር አገልግሎት

## ፳. ስለ ቁጥጥር

፩/ ሚኒስቴሩ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ሠራተኞችን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ የሥራ ውል ለፀደቀላቸው ልዩ መታወቂያ ይሰጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ መሠረት የተጣለበትን ግዴታና ኃላፊነት እየተወጣ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ የሥራ

፲ሺ፲፻፸፩ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ይመድባል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተመደበ ማንኛውም የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፦

ሀ) ለኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ ወይም ከመታደሱ ወይም ነባሩን የቢሮ አድራሻ ከመለወጡ በፊት የተሟላ ቢሮ፣ የምልመላ ሥርዓትና የቅድመ ቅጥር ገለፃና የምክር አገልግሎት መስጫ ቦታና ባለሙያ ማሟላቱን የማረጋገጥ፤

ለ) በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን የማረጋገጥ

ሐ) በኤጀንሲ አማካይነት ወደ ውጭ አገር ለሥራ ተቀጥረው ለሚሄዱ ሠራተኞች ስለአጠቃላይ የሥራ ሁኔታና ስለሚሄዱ ባቸው አገሮች ሁኔታ መግለጫ እና

any agency whether it discharges its obligations and responsibilities provided for in this Proclamation in.

3/ Any labour inspector assigned by the Ministry or the appropriate authority pursuant to sub-article (2) of this Article shall have the following powers and duties:

a) ascertain that an Agency has possessed fully equipped office, sufficient and appropriate space and necessary expertise for conducting recruitment process, pre employ ment orientation and counseling services before the issuance or renewal of license or change of the existing office;

b) Ensure that the agency has in place automated data base system.

c) ensure that the agency has given orientation on general conditions of work, situation of receiving countries, and pre-employment and pre-departure orientation and counseling services to workers destined for overseas employment;

d) undertake appropriate investigation whenever he is aware or notified that an Agency has contravened this Proclamation or regulations or directives issued hereunder;

e) undertake monitoring so as to prevent illegal recruitment and deployment of workers;

f) enter the office of any agency, at any time during working hours, and examine necessary documents, records, books of accounts and other similar documents, and make inquires.

4/ The labour inspector while conducting inspection pursuant to sub-article (3) of this Article shall keep with or show his identity card issued to him by the Ministry or the appropriate authority.

5/ The labour inspector shall submit, the findings of the inspection conducted pursuant to sub-article (3) of this Article to the Ministry or the appropriate authority

የቅድመ-ቅጥርና ቅድመ-ጉዞ ትምህርትና ምክር አገልግሎት የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ፤

መ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ኤጀንሲው መተላለፉን ራሱ ሲረዳ ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ተገቢውን ማጣራት የማከናወን፤

ሠ) ሕገ ወጥ የሠራተኛ ምልመላና ቅጥር ተግባር እንዳይከናወን ቁጥጥር የማካሄድ፤

ረ) በኤጀንሲው ቢሮ በማንኛውም የሥራ ሰዓት በመገኘት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን፣ መዝገቦችን፣ የሂሳብ መዛግብቶችንና የመሳሰ ሉትን የመመርመርና ጥያቄ የማቅረብ ፡፡

፬/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ቁጥጥር ሲያካሂድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን የተሰጠውን መታወቂያ ይዞ መገኘት እና ማሳየት አለበት፡፡

፭/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ባካሄደው ቁጥጥር የደረሰበትን ግኝትና ሊወሰድ ስለሚገባው ሕጋዊ እርምጃ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፲ሺ፫፻፸፪

፮/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ቁጥጥር የሚካሄድበትን የአፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፯/ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪው ሥልጣኑን አለአግባብ በመጠቀም ለሚፈፅመው ድርጊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፰/ ለሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ተግባር መሳካት ማንኛውም ኤጀንሲ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## በኤጀንሲ ስለሚሰጥ የሥራ ስምሪት አገልግሎት

### ንዑስ ክፍል አንድ
### ስለፈቃድ፣ ለፈቃድ ብቁ ስለመሆንና ስላለመሆን

**፳፩. ፈቃድ ስለማስፈለጉ**

together with his recommendations on legal measures to be taken.

6/ The Ministry may issue directive on the procedures of conducting inspections pursuant to sub-article (3) of this Article.

7/ The inspector shall be held accountable for abuse of power in accordance with appropriate law.

8/ Any Agency shall have obligation to cooperate for the proper implementation of the responsibility of labour inspector.

## PART FOUR
## OVERSEAS EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE THROUGH AN AGENCY
### SECTION ONE
### LICENSE, ELIGIBILITY AND NON-ELIGIBILITY FOR LICENSE

**21. Requirement of a License**

1/ Any person who desires to operate an Agency shall obtain a license from the Ministry.

2/ Any person who wishes to operate in more than one country by issuing license pursuant to sub-article (1) of this Article shall obtain a separate license for each country of operation.

**22. Eligibility to Obtain License**

In order to obtain a license of Agency:

1/ where the applicant is sole proprietor, he shall be an Ethiopian citizen and have operating capital not less than Birr one million;

2/ where the applicant is a business organization, the sole objective shall be overseas employment exchange service and all its members are Ethiopian citizens and have paid up operating capital not less than Birr one million in shares or contributions.

3/ the applicant shall not be a person prohibited pursuant to this Proclamation or other relevant laws not to operate overseas employment exchange service.

https://ethiodata.et/

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ኤጀንሲ ሆኖ ለመሥራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ በማውጣት ከአንድ አገር በላይ ለመሥራት የሚፈልግ ሰው ለእያንዳንዱ አገር ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

## ፳፪. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

ኤጀንሲ ሆኖ ፈቃድ ለማግኘት፦

፩/ አመልካቹ ግለሰብ ድርጅት ከሆነ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እና ከአንድ ሚሊዮን ብር ያላነሰ ካፒታል ያለው፣

፪/ አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ የተቋቋመበት ዓላማ በውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት አገልግሎት ለመስጠት ብቻ የተቋቋመ፣ የንግድ ማህበሩ አባላት በሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው እና ከአንድ ሚሊዮን ብር ያላነሰ የተዋጣ አክሲዮን ወይም መዋጮ ያለው፣

፫/ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች መሠረት በውጭ አገር ሥራ ስምሪት ዘርፍ እንዳይሰማራ ያልተከለከለ፣

መሆን ይኖርበታል፡፡

## ፳፫. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስላለመሆን

ከዚህ በታች የተመለከቱት ፈቃድ ለማግኘት ብቁ አይሆኑም፦

፳ሺ፰፻፸፫

፩/ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ፦

ሀ) ፈቃዱ የተሰረዘበት ማንኛውም ኤጀንሲ፣ አባሎቹ እና ኤጀንሲው የአክሲዮን ማህበር ከሆነ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፤

ለ) የሠራተኞች መብት፣ ደህንነት እና ክብር በመጣሱ ምክንያት ለቀረቡ አቤቱታዎች መፍትሔ ባለመስጠቱ ፈቃዱ የተሰረዘበት ፤

ሐ) ከሦስት ጊዜ በላይ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የፈቃድ ስረዛ ቅድመ ማስጠንቀቂያ በጽሁፍ የተሰጠው

## 23. Non-eligibility to Obtain License

The following shall not be eligible to obtain license:

1/ for contravention of the Proclamation No. 632/2009, regulations or directive issued there-under;

a) any Agency, its members or in cases where the Agency is a share company, the Board of Directors whose license had been revoked;

b) any agency or its members whose license had been revoked for failure to provide remedies for complaint against it for violations of the rights, safety and dignity of workers;

c) any agency whose license has been suspended for more than three times or written notice for revocation of license has been served on;

2/ an individual accused and sentenced by the court of law for his engagement in human trafficking, smuggling of migrants, organized crime, terrorism acitivity, transfer of narcotic substances or money laundering or individual charged for the crime and whose case is pending before a court of law until decision is rendered;

3/ travel agency, ticket office of airlines or employee of the travel agency or ticket office of airlines, transistor or seaman;

4/ any official or employee in the Ministry, the Appropriate authority, Ministry of Foreign Affairs, Main Department for Immigration and Citizenship, Police Commission or any governmental organ entrusted to implement this Proclamation or Ethiopian community overseas in leadership position or the families of these individuals.

## SECTION TWO
## ISSUANCE OF LICENSE

## 24. Requirements to Obtain License

Any applicant who is eligible pursuant to Article 22 of this Proclamation shall fill the application form prepared for such purpose and submit it together with the following

https://ethiodata.et/

ማንኛውም ኤጀንሲና አባሎቹ፤

፪/ በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፣ስደተኞችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር በተደራጁ ወንጀሎች፣ በሽብርተኝነት በአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር ወይም በሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል ተከሶ በፍርድ ቤት የተቀጣ ሰው ወይም በወንጀል ድርጊቱ ተከሶ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለ ሰው ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ፤

፫/ የጉዞ ወኪል እና የአየር መንገድ ቲኬት ሽያጭ ቢሮ ወይም የወኪሉ ወይም የቢሮው ሠራተኛ፣ ትራንዚተር ወይም መርከበኛ፤

፬/ የሚኒስቴሩ፣ አግባብ ያለው ባለሥልጣን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ፣ የፖሊስ ኮሚሽን ወይም ይህን አዋጅ በቀጥታ የሚያስፈጽም የመንግሥት አካል ማንኛውም የሥራ ኃላፊ፣ ሠራተኛ ወይም በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ አመራር አባል እና የእነዚሁ ቤተሰቦች፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**
**ስለፈቃድ አሰጣጥ**

**፳፬. ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለባቸው መሥፈርቶች**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ብቁ የሆነ ማንኛውም አመልካች ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አሟልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፦

፩/ በኤጀንሲነት ሥራ ለመሰማራት የሚያስችለው የንግድ ምዝገባ እና የንግድ ስያሜ የምስክር
፲ሺ፫፻፸፬ ወረቀት፤

፪/ አመልካቹ ሥራውን የሚያካሂደው በንግድ ማህበርነት ከሆነ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽሕፈት ቤት የተረጋገጠ የመመሥረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ዋና ቅጂ፤

፫/ አመልካች ፈቃድ ለማውጣት የጠየቀው በግል ከሆነ ግለሰቡ፣ በሽርክና ማህበርነት ከሆነ የማህበሩ አባላት ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወይም በአክሲዮን ማኅበር ከሆነ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና አመራር አካላት

documents:

1/ certificate of Business Registration and Trade Name enabling the applicant to operate as an Agency;

2/ where the applicant operates the activity as a business organization, copies of its Memorandum of Association and Articles of Associations authenticated by the Document Authentication and Registration Office;

3/ certificate of clearance from Police confirming that the individual applicant, if he is a sole proprietor, or its members if it is partnership and Board of Directors, management bodies, as well as the officials and employees, if the applicant is a private limited company or share company, if any, were not involved in crimes specified under Article 23 (2) of this Proclamation;

4/ a chart showing the organizational structure of the Agency together with list of required manpower and educational qualifications; job position, personal history and two passport size photographs of each official and employee;

5/ office address of the applicant and certificate of ownership if he is the owner of office or the original copy of the contract of lease authenticated by the Document Authentication and Registration Office if the office is leased one;

6/ verification document to the effect that the security bond pursuant to Article 60 (1) of this Proclamation is complied with;

7/ confirmation document that specifies the general manager has at least first degree and three years' management work experience;

8/ certificate showing the attendance of the owner and the general manager in pre-license training, if the activity is operated by sole proprietor; or if it is operated by a business organization, a certificate showing the attendance of the members and management members of the business organization in pre-license training;

9/ In the country of destination:

a) that the applicant has opened a decent

እንዲሁም የሥራ ኃላፊዎችና ተቀጣሪ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፫(፪) ከተመለከቱ ወንጀሎች ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ከፖሊስ የተሰጠ ማስረጃ፣

፬/ የአደረጃጀት መዋቅሩን የሚያሳይ ቻርት፣ ለሥራ የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ዝርዝርና የትምህርት ማስረጃ፣ የእያንዳንዱ ኃላፊና ሠራተኛ የሥራ መደብ፣ የግል ታሪክ፣ የፓስፖርት መጠን ያላቸው ሁለት ጉርድ ፎቶግራፎች፤

፭/ የአመልካቹ የሥራ ቦታ አድራሻና የቢሮው ይዞታ የራስ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ወይም ኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽሕፈት ቤት የተረጋገጠ ዋና ቅጂ፤

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳(፩) የተመለከተውን የዋስትና ግዴታ ማሟላቱን የሚገልፅ ማረጋገጫ ሰነድ፤

፯/ ሥራ አስኪያጁ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በሥራ አመራር ሦስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰነድ፤

፰/ ሥራው የሚቋቋመው በግለሰብ ከሆነ ባለቤቱ እና ሥራ አስኪያጁ፣ በንግድ ማህበርነት ከሆነ የማኅበሩ አባላትና የአመራር አካላት በቅድመ ፈቃድ ሥልጠና ላይ ስለመሳተፋቸው የሚገልፅ የምስክር ወረቀት፣

፱/ ሠራተኛን በሚልክበት አገር ፦

ሀ) የተሟላ ቢሮ ስለመክፈቱ ወይም የተቀባይ አገር ዜግነት ያለውና በአገሩ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በሥራና ሠራተኛ አገናኝነት ሥራ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል ፈቃድ ያለውን ሰው በውክልና ስለመሰየሙ የተረጋገጠ ማስረጃ፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ተወካይም ውክልናውን ስለመቀበሉ በሚመለከተው ሚሲዮን ወይም በተቀባዩ አገር ሚሲዮን ከሌለ አዲስ አበባ በሚገኘው የተቀባዩ አገር ሚሲዮን እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ሰነድ ማስረጃ፣እና

office or has represented a citizen of the receiving country duly licensed to engage in overseas employment exchange services and produced a verification document showing same;

b) that the delegate represented pursuant to paragraph (a) of this sub-article has accepted the representation and this is verified by the Ethiopian Mission or if there is no Ethiopian Mission in the country of destination through the latter's mission here in Ethiopia and confirmed by the Ministry of Foreign Affairs and produced a verification document showing same;

c) that the applicant has a facility for providing temporary food and sheltering services to the workers and to this effect a confirmation letter by the Mission and the Ministry of Foreign Affairs produced;

10/ confirmation letter issued by appropriate organ that the applicant is authorized to freely enter into and exit from the receiving country;

11/ Tax clearance certificate

12/ receipt showing payment of license fee;

13/ other evidences to be prescribed by the directive of the Ministry, as the case may be.

**25. Issuance of License**

Whenever the Ministry ensures that the requirements for issuing license as per this Proclamation are met, it shall, within five working days, issue the license to the applicant. If the application for license is denied, such denial shall, within five working days, be communicated in writing to the applicant.

**26. Validity of License**

A license issued pursuant to Article 25 of this Proclamation shall remain valid for one year.

**27. Display of License in Conspicuous Place**

ሐ) ለሠራተኛው ጊዜያዊ የምግብና የመጠለያ አገልግሎት መስጫ ቦታ ያዘጋጀ ስለመሆኑ በሚመለከተው ሚሲዮንና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ደብዳቤ፣

፲/አመልካቹ ሠራተኛ ወደሚልክበት አገር በነፃነት መግባትና መውጣት የሚችል ስለመሆኑ በሚመለከተው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ፤

፲፩/ቀደም ሲል ፈቃድ ተሰጥቶት ሲሰራ በነበረበት ጊዜ የሚፈለግበትን ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ማስረጃ፤

፲፪/ የፈቃድ ክፍያ መፈጸሙን የሚያሳይ ደረሰኝ፤

፲፫/ እንደ አስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች ማስረጃዎች፡፡

## ፳፭. ፈቃድ ስለመስጠት

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያበቁ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ ይሰጣል፤ የቀረበው የፈቃድ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ከሆነም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያስታውቃል፡፡

## ፳፮. ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል፡፡

## ፳፯. ፈቃድን በግልፅ ቦታ ስለማስቀመጥ

ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ በከፈተው ቢሮ ውስጥ ግልፅ ሆኖ በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

፷ሺ፰፻፸፮

## ፳፰. የሥራ ፈቃድ ማስተላለፍ እና ከአንድ ኤጀንሲ በላይ መሳተፍ የተከለከለ ስለመሆኑ

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ ለሌላ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማስተላለፍ ክልክል ነው፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ከአንድ ኤጀንሲ በላይ ባለቤት፣ የሽርክና ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ

Any Agency shall display the license issued to it in accordance with this Proclamation in its office in a conspicuous place.

## 28. Non-transferability of License and Prohibition of Engagement in more than one Agency

1/ No Agency shall, directly or indirectly, transfer to any other person the license issued to him by the Ministry.

2/ Any person can not operate in more than one Agency directly or indirectly as owner or a member of partner ship or private limited campany, Board of directors, General manager or an employee.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, in case of death of a sole proprietor, the license may devolve to his legitimate heirs, upon their request, for the mere purpose of preventing disruption in protecting the rights, safety and dignity of workers and winding up of operation of the business in accordance with this Proclamation.

4/ Where the heirs specified under sub-article (3) of this Article seek to resume the operation of the Agency, the Ministry may transfer the license to them upon being satisfied that they meet the requirements.

## 29. Notification of Change of Management or an Employee

Any Agency shall, up on making change to its board of directors or general manager or recruit or dismiss any employee, notify same to the Ministry or the Appropriate authority within 10 working days.

## 30. Making Management Personnel Public

Any Agency shall, publicize changes of its general manager or its board of directors, within seven working days through a newspaper of wider circulation, radio and television and notify the same to the Ministry or the appropriate authority.

## 31. Opening Additional Local Offices

የግል ማህበር አባል፣የቦርድ አመራር፣ሥራ አስኪያጅ ወይም ሠራተኛ ሆኖ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ መሥራት አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተመለከተው ቢኖርም ኤጀንሲው በግለሰብ የተቋቋመ ከሆነና ግለሰቡ ከሞተ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የተላኩ ዜጎች መብት፣ ደህንነትና ክብር ለማስጠበቅ ሲባል ብቻ ሥራውን ላለማስተጓጎልና ለማጠና ቀቅ በግለሰቡ ሕጋዊ ወራሾች ጠያቂነት የሥራ ፈቃዱ ለነዚህ ወራሾች ሊተላለፍ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከቱት ወራሾች በዘላቂነት ሥራውን ማስቀጠል ከፈለጉ ሚኒስቴሩ ጠያቂዎቹ ለፈቃድ ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ፈቃዱን ሊያስተላልፍላቸው ይችላል፡፡

**፳፱. <u>የአመራር ወይም የሠራተኛ ለውጥ ስለማሳወቅ</u>**

ማንኛውም ኤጀንሲ የቦርድ አመራር ወይም የሥራ አስኪያጅ ለውጥ ሲያደርግ ወይም ሠራተኛን ሲቀጥር ወይም ሲያሰናብት ይህንኑ እንደአግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

**፴. <u>አመራርን ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ</u>**

ማንኛውም ኤጀንሲ በሥራ አስኪያጁ ወይም በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ላይ ያደረገውን ለውጥ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ፣ሬዲዮና ቴሌቪዥን በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**፴፩. <u>በአገር ውስጥ ተጨማሪ ቢሮ ስለመክፈት</u>**

ማንኛውም ኤጀንሲ ለሥራ ማካሄጃ በአገር ውስጥ ተጨማሪ ቢሮ መክፈት ሲፈልግ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡



**፴፪. <u>የቢሮ አድራሻ ለውጥ ስለማድረግና ስለማሳወቅ</u>**

Any Agency shall obtain permission from the Ministry or appropriate authority to open additional local office.

**32. <u>Change of Business Address and Notification</u>**

An Agency:

1/ may only change its business address after the Ministry or the appropriate authority verifies and approves that the office complies with the requirements specified under Article 24 (5) of this Proclamation;

2/ shall, within seven working days publish the change of business address effected up on approval pursuant to sub-article (1) of this Article in a newspaper having wider circulation and submit evidence of same to the Ministry or the Appropriate authority.

**33. <u>Renewal of License</u>**

1/ A license issued in accordance with this Proclamation shall be renewed every year.

2/ Any Agency one month prior to the expiry of the period specified under sub-article (1) of this Article shall, in order to renew a license, fill an application form and submit it to the Ministry with the following documents:

a) evidence of the deposit of a security bond pursuant to Article 60 (1) of this Proclamation;

b) financial statement audited by external auditor and evidence showing that the Agency has settled its tax liability;

c) clearance from Police showing that those persons mentioned under Article 24 (3) of this Proclamation are free from any criminal activity specified under Article 23 (2) of this proclamation;

d) evidence of renewed license of its foreign representative;

e) general report that indicates the status of deployed and returned overseas workers;

f) other documents specified in the directives of the Ministry.

ማንኛውም ኤጀንሲ ፦

፩/ የቢሮ አድራሻ ለውጥ ማድረግ የሚችለው ቢሮው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬(፭) የተመለከተው ማሟላቱን እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን አረጋግጦ ሲፈቅድለት ብቻ ነው፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተፈቅዶ የተፈፀመውን የቢሮ አድራሻ ለውጥ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ላይ ለሕዝብ በማሳወቅ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስረጃውን ማቅረብ አለበት፡፡

፴፫. ስለ ፈቃድ ዕድሳት

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ በየዓመቱ የሚታደስ ይሆናል፡፡

፪/ ማንኛውም ኤጀንሲ ፈቃድ ለማደስ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለዚሁ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል ፦

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ (፩) የተመለከተውን የዋስትና ግዴታ ማሟላቱን የሚያሳይ ማስረጃ፤

ለ) በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የዘመኑ የሂሳብ ሪፖርትና ግብር የተከፈለ ስለ መሆኑ ማስረጃ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬(፫) የተዘረዘሩት አካላት በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ ፳፫(፪) መሠረት ከወንጀል ነፃ ለመሆናቸው ከፖሊስ ማስረጃ፤

መ/ በተቀባይ አገር የተሰየመው ወኪል የታደሰ የንግድ ፈቃድ ማስረጃዎች፤

ሠ) ለሥራ ወደ ውጭ አገር ስላሰማራቸውና ስለተመለሱት ሰራተኞች የሚገልፅ አጠቃላይ ሪፖርት፤

ረ) በሚኒስቴሩ መመሪያ የተወሰኑ ሌሎች ማስረጃዎች፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለማደስ የሚያበቁ ሁኔታዎች መሟላታቸውን እንዳረጋገጠ የፈቃድ ዕድሳት ክፍያ እንዲፈጽም በማድረግ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ ያድሳል፤ የቀረበው የፈቃድ ዕድሳት ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ከሆነም

3/ Where the Ministry is satisfied that the Agency has met the requirements for license renewal, up on causing to pay license renewal fee, shall issue the renewed license within three working days; where the application for license renewal is denied, such denial shall be communicated in writing to the applicant within the same timeline.

4/ The license not renewed within the validity period specified under Article 26 of this Proclamation shall be suspended.

5/ Where an Agency fails to renew its license in due time, its license may be renewed within three months following the expiry date, up on payment of 20% additional fee for the first month; 40% additional fee for the second month and 60% additional fee for the third month in the form of penalty.

34. Incentive Scheme

The Ministry may issue directive on incentive scheme to evaluate and reward Agencies involved in the sector and achieve good performance.

## SECTION THREE

## EMPLOYMENT EXCHANGE SERVICE

35. Advertisement for Overseas Employment

1/ Any Agency shall, as the case may be, submit to the Ministry or the appropriate authority to register and get approval before advertizing any overseas job vacancy.

2/ Job vacancy advertisement through any mass media, shall indicate the following:

a) the name of the Agency, address and license number issued to it by the Ministry and the authorized country for sending workers;

b) number of vacant job positions, required qualification, wage rate, duration of employment, country of destination and worksite and other necessary information;

c) a declaration that the Agency does

በዚሁ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያስታውቃል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፳፯ መሠረት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲጠናቀቅ ያልታደሰ የኤጀንሲ ፈቃድ ታግዶ ይቆያል፡፡

፭/ ኤጀንሲው ፈቃዱን በወቅቱ ሳያሳድስ የቀረ እንደሆነ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካበቃበት በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ውስጥ ለመጀመሪያው ወር የዕድሳት ክፍያውን ሃያ በመቶ፣ ለሁለተኛው ወር አርባ በመቶ እና ለሦስተኛው ወር ስልሳ በመቶ ቅጣት በተጨማሪ በመክፈል ፈቃዱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡

**፴፬. <u>ስለ ማበረታቻ ሥርዓት</u>**

ሚኒስቴሩ በዘርፉ የተሰማሩ ኤጀንሲዎችን አፈፃፀም በመገምገም የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግቡትን ለማበረታታት የማበረታቻ አሠጣጥ ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>**

**<u>ስለ ሥራ ስምሪት አገልግሎት</u>**

**፴፭. <u>ስለውጭ አገር ሥራ ማስታወቂያ</u>**

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ ስለውጭ አገር ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ከማውጣቱ በፊት እንደአግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በማቅረብ ማስመዝገብና ማፀደቅ ይኖርበታል፡፡

፪/ ክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ በማናቸውም የመገናኛ ብዙኃን ሲወጣ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡-

ሀ) የኤጀንሲውን ስም፣ አድራሻ፣ በሚኒስቴሩ የተሰጠውን ፈቃድ ቁጥር እና ሠራተኛ ለመላክ የተፈቀደለት አገር፤

ለ) ስለተገኘው ክፍት የሥራ መደብና ዓ ብዛት፣ተፈላጊ ችሎታ፣ የደመወዝ መጠን የቅጥር ቆይታ ጊዜ፣ሥራው የተገኘበት አገር፣ቦታ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች፤

ሐ) ኤጀንሲው ለሚሰጠው ማንኛውም አገልግሎት ሰራተኛውን ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ የማያስከፍል ስለመሆኑ መግለጫ፡፡

not collect service charge from the worker for any service it provides.

**36. <u>Recruitment of Worker</u>**

1/ Any Agency shall conduct worker recruitment only within the premises of its office.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, where the recruitment requires substantial work force, the Ministry or the appropriate authority may authorize a temporary recruitment venue the particulars of which shall be prescribed in the directives of the Ministry.

**37. <u>Approval of Contract of Employment</u>**

1/ An Agency shall submit for approval a contract of employment signed by the employer, the Agency and the worker which is drawn up in accordance with the model contract of the Ministry and up on fulfilling other requirements specified in the directive issued by the Ministry.

2/ The signature of the employer in the contract of employment specified under sub-article (1) of this Article and other documents attached to shall be verified by the appropriate Mission and the Ministry of Foreign Affairs.

3/ Where the Ministry is satisfied that the conditions stipulated under sub-articles (1) and (2) of this Article are met, it shall approve and register the contract of employment with in a time prescribed by the directive.

**38. <u>Deployment of Worker and Reporting</u>**

Any Agency shall:

1/ deploy the worker within one month after the approval of the contract of employment;

2/ notify to the Ethiopian Mission or Consular office in the country of destination and cause registration of deployed workers within 15 days with; ensure that the worker has obtained work permit and residence permit and report the

**፴፮. ስለ ሠራተኛ ምልመላ**

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ የሠራተኛ ምልመላ ማከናወን የሚችለው በከፈተው ቢሮ ውስጥ ብቻ መሆን አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የሚፈጸመው የሠራተኛ ምልመላ ብዙ የሰው ኃይል የሚጠይቅ ከሆነ ጊዜያዊ ምልመላ የሚካሄድበትን ቦታ እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሊፈቅድ ይችላል፣ ዝርዝር አፈፃፀሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፴፯. የሥራ ውልን ስለማፅደቅ**

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ ሚኒስቴሩ ያወጣውን ሞዴል የሥራ ውል መሠረት በማድረግ አሠሪ፣ ኤጀንሲው እና ሠራተኛው የፈረሙበትን የሥራ ውል እና ሌሎች ሚኒስቴሩ በመመሪያ የወሰና ቸውን መሥፈርቶች በማሟላት እንዲፀድቅ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው የሥራ ውል የተመለከተው የአሠሪ ፊርማና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች ትክክለኛነት በሚመለ ከተው ሚሲዮን እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን እንዳረጋገጠ በመመሪያ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የቀረበውን የሥራ ውል በማፅደቅ ይመዘግባል፡፡

**፴፰. ሠራተኛን ለሥራ ስለማሰማራትና ስለማሳወቅ**

ማንኛውም ኤጀንሲ ፡-

፩/ የሥራ ውል በፀደቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ሠራተኛን ለሥራ ማሰማራት፣

፪/ ወደ ውጭ አገር ለሥራ የላከውን ሠራተኛ በሚሄድበት አገር ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽሕፈት ቤት በ፲፭ ቀናት ውስጥ አሳውቆ የማስመዝገብ፣ የሥራ ፈቃድና የመኖሪያ ፈቃድ ስለማግኘቱ የማረጋገጥና ይህንኑ መረጃ አሟልቶ

same to the Ministry.

**39. Revocation of Contract of Employment**

Where the Agency fails to deploy the worker within the time-limit prescribed under Article 38 (1) of this Proclamation, it shall notify along with reason to the Ministry within one month for the revocation of the approved contract of employment.

**40. Joint and Several Liability**

Where the contract of employment of a worker is breached, the Agency and the employer shall be held jointly and severally liable.

## PART FIVE
## VIOLATION AND CORRESPONDING MEASURE
## SECTION ONE
## VIOLATIONS BY AN AGENCY AND CORRESPONDING CORRECTIVE MEASURES

**41. Power to Decide Administrative Matters**

The Ministry or the appropriate authority shall have power to hear and decide administrative matters involving or arising out of violations of this Proclamation, and Regulations and Directives issued hereunder including refund of fees illegitimately collected from workers.

**42. Type of Contraventions**

1/ The contravention of sub-article (2) or (3) of this Article shall entail suspension or revocation measure against the license of an Agency.

2/ The following contraventions shall entail suspension of a license:

a) obstruction or attempt to obstruct the activities of labour inspector assigned for the purpose of inspection by the Ministry or appropriate authority;

b) appointing a general manager or

ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣

ይኖርበታል፡፡

፰ሺ፰፻፹

**፴፱. የሥራ ውልን ስለማሰረዝ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰(፩) በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ኤጀንሲው ሠራተኛን ወደ ሥራ ማሰማራት ካልቻለ የጸደቀው የሥራ ውል እንዲሰረዝ ከነምክንያቱ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፵. ስለ የጋራ እና የተናጠል ኃላፊነት**

ከሠራተኛ ጋር የተደረገ የሥራ ውል ቢጣስ ኤጀንሲውና አሠሪው ለሠራተኛው መብት በጋራና በተናጠል ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለጥፋት እና ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ

### ንዑስ ክፍል አንድ
### በኤጀንሲ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶችና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

**፵፩. አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመወሰን ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኤጀንሲው ከሠራተኛ ያለአግባብ የተቀበለውን ገንዘብ የማስመለስ ጥያቄን ጨምሮ ይህን አዋጅና አዋጁን መሠረት አድርጎ የወጣ ደንብና መመሪያ በመጣሱ ምክንያት የሚነሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመስማትና የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፵፪. የጥፋት ዓይነቶች**

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) ከተመለከቱት ጥፋቶች አንዱን በፈፀመ ኤጀንሲ ላይ የፈቃድ ዕገዳ ወይም ስረዛ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

፪/ የሚከተሉት የፈቃድ ዕገዳን የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው ፦

ሀ) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ቁጥጥር እንዲያካሂድ የመደበ

members of board of directors or recruit an employee without prior notice to the Ministry or the appropriate authority;

c) recruiting a worker not completed at least grade eight and who does not possess Certificate of Occupational Competence from an authorized organ;

d) influencing or attempting to influence any employer not to employ a worker other than those registered by his own Agency;

e) failure, without good cause, to deploy a worker within the legally prescribed time limit;

f) failure to provide remedy for applications pertaining to violations of workers' rights, safety and dignity;

g) disregard of orders and notices issued by the Ministry or the appropriate authority or failure to follow other legal processes;

h) failure to submit periodic reports required by the Ministry or the appropriate authority which are related to deployed workers, vacant job positions, foreign currency earned by the Agency in the form of commission for its services;

i) failure to submit report on the lists of workers who are terminated from employment due to various reasons and other similar information requested by the Ministry or the appropriate authority;

j) failure to display its license in a conspicuous place of its office;

k) failure to provide adequate service as required by this Proclamation;

l) withholding of the worker's wage or his remittances;

m) failure to refund expenses of worker who was not deployed for reason not imputable to him;

https://ethiodata.et/

ውን የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ ሥራ ማሰናከል ወይም ለማሰናከል መሞከር፤

ለ) ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳያሳውቅ ሥራ አስኪያጅ ወይም የአመራር ቦርድ አባል መሾም ወይም ሠራተኛ መቅጠር፤

ሐ) ቢያንስ የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ያላጠናቀቀ እና አግባብ ካለው የምዘና ማዕከል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ያልያዘን ሠራተኛ መመልመል፤

መ) በራሱ ኤጀንሲ የተመዘገበን ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም አሰሪ ሰራተኛ እንዳይቀጥር ተፅዕኖ ማሳደር ወይም ተፅዕኖ ለማሳደር መሞከር፤

ሠ) ያለበቂ ምክንያት ሠራተኛን በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለሥራ ማሰማራት አለመቻል፤

ረ) የላካቸው ሠራተኞች መብት፣ ደህንነት እና ክብር በመጣሱ ምክንያት ለሚቀርበው አቤቱታ መፍትሄ አለመስጠት፤

ሰ) በሕግ አግባብ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን የሚሰጣቸውን ትዕዛዞችና ማስታወቂያዎች አለመፈጸም እና ሌሎች አሰራሮችን አለመከተል፤

ሸ) ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚጠይቃቸውን ለሥራ የተሰማሩ ሠራተኞች ወቅታዊ ሪፖርቶች፣ የተገኙ ክፍት የሥራ ቦታዎች፣ በሥራው ምክንያት ከውጭ አገር በኮሚሽን መልክ ገቢ የተደረገለትን የውጭ አገር ምንዛሪ ገንዘብ መጠን በየወቅቱ አለማሳወቅ፤

ቀ) በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራቸው የተለዩ ሠራተኞች ዝርዝር እና ሌሎች ተመሳሳይ መረጃዎችን በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚጠየቁ መረጃዎችን አለማቅረብ፤

በ) ፈቃዱን ሥራውን በሚያካሂድበት ቢሮ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ሊታይ በሚችልበት ቦታ አለማኖር፤

ተ) በዚህ አዋጅ መሠረት መስጠት የሚገባውን አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ



n) failure to provide pre-departure orientation and counseling service to workers destined for overseas employment;

o) failure to immediately verify and report to the Ministry on employment bodily injury sustained by or death of workers on overseas employment together with the reasons thereof and the remedial measure undertaken;

p) failure to comply with Article 60(4) of this Proclamation.

3/ The following contraventions shall entail revocation of a license:

a) the direct or indirect engagement of the owner, general manager or employee of an Agency licensed as sole proprietor as a manager or as an employee in a travel agency or air ticket office management;

b) for an Agency established in the form of:

(1) partnership or private limited company when its members, general manager or employee; or

(2) share company when its board of directors or general manager or employee,

a manager or an employee in travel agency or in air ticket office engage directly or indirectly in activities;

c) failure to renew license within the period prescribed under Article 33 (5) of this Proclamation;

d) recruitment and deployment of a worker who is below the age of eighteen years;

e) obtaining or renewing license based on falsified evidence;

f) recruiting or deploying workers to a destination where there is no bilateral agreement between Ethiopia and the receiving country or to a destination where the Ministry has put prohibition;

https://ethiodata.et/

አለመስጠት፤

ቸ) የሠራተኛውን ደመወዝ ወይም ሠራተኛው ወደ አገሩ የሚልከውን ገንዘብ መያዝ፤

ኀ) በራሱ ባልሆነ ምክንያት ወደ ሥራ ያልተሰማራ ሠራተኛ ያወጣውን ወጪ ያለመተካት፤

ነ) ለሠራተኞች የቅድመ-ጉዞ ገለፃ እና የምክር አገልግሎት አለመስጠት፤

፫ሺ፫፻፹፪

ኘ) ሠራተኛው ለሥራ በሄደበት አገር የአካል ጉዳት ወይም የሞት አደጋ ሲደርስበት የአደጋውን መንስኤና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ወዲያውኑ በማጣራት ለሚኒስቴሩ አለማሳወቅ፤

አ) በዚህአዋጅ በአንቀጽ ፳(፬) የተመለከተውን አለመፈጸም፡፡

፫/ የሚከተሉት የፈቃድ ስረዛን የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው ፦

ሀ) በግለሰብ የተቋቋመ ኤጀንሲ ወይም ባለቤቱ፣ ሥራ አስኪያጁ ወይም ሠራተኛው በጉዞ ወኪል ወይም የአየር መንገድ ቲኬት ቢሮ ውስጥ በአመራር ወይም በሠራተኛ ነት፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ሆኖ መገኘት፤

ለ) ፈቃድ የተሰጠው ኤጀንሲ የተቋቋመው

፦

(፩) በሽርክና ወይም ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ የማህበሩ አባላት፣ ሥራ አስኪያጁ ወይም ሠራተኛው፤

(፪) በአክሲዮን ማህበር ከሆነ የማህበሩ የዳይሬክተሮች የቦርድ አባላቱ፣ ሥራ አስኪያጁ ወይም ሠራተኛው፤

በጉዞ ወኪል ወይም የአየር መንገድ ትኬት ቢሮ ውስጥ በአመራር ወይም በሠራተኛነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳታፊ ሆኖ መገኘት

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫(፰) መሠረት ፈቃድ በወቅቱ አለማሳደስ፤

መ) ዕድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነን ሰው

g) recruiting or deploying workers to a service that adversely affects public health or morality or damages the country's image;

h) transferring or changing ownership of a license in contravention of the provisions of this Proclamation;

i) receiving fee, in cash or in kind, from a worker in return for overseas employment exchange service;

j) deployment of a worker before the approval of the contract of employ ment by the Ministry;

k) sending a worker to a destination other than what is stipulated in his contract of employment;

l) engaging in a type of service, place of work or country apart from those stipulated in the license;

m) assigning a worker to an employer other than that mentioned in the approved contract of employment;

n) engaging a person, in an Agency's business, who is prohibited from overseas employment exchange service by this Proclamation, any other law or by the decision of court;

o) furnishing falsified evidence or document or advertisement in order to recruit or deploy a worker;

p) substituting or replacing the approved contract of employment by another without notifying to and approval of the Ministry;

q) withholding and prohibiting travel document and other information of the worker before or after deployment;

r) intentional falsifying or changing worker's travel document;

s) compelling a worker to relinquish his rights and benefits through fraudulent practice or duress.

## 43. Submission of Complaint

1/ Any victim worker or his representative

መመልመልና ለሥራ ማሰማራት፤

ሠ) ፈቃድን በተሳሳተ መረጃ ማግኘት ወይም ማሳደስ፤

ረ) በኢትዮጵያ እና በተቀባይ አገር መካከል የሠራተኛ ቅጥር የሁለትዮሽ ስምምነት ከተፈፀመበት አገር ውጭ ወይም ሚኒስቴሩ ሠራተኛ ለሥራ እንዳይሰማራ ወደ ከለከለበት አገር ሠራተኛን ለመላክ መመልመል ወይም ማሰማራት፤

ሰ) የሕዝብን ጤና ወይም ሞራል በሚጎዳ ወይም የአገሪቷን ክብርና ገፅታ ለሚያጎ ድፍ ሥራ ሠራተኛን መመልመል ወይም ማሰማራት፤

፲ሺ፫፻፹፬

ሸ) የተሰጠውን ፈቃድ በዚህ አዋጅ ከተመለ ከተው ውጭ ለሌላ ማስተላለፍ ወይም ባለቤትነትን መቀየር፤

ቀ) የሥራ ስምሪት አገልግሎትን ምክንያት በማድረግ ከሠራተኛ ገንዘብ በጥሬም ሆነ በዓይነት መቀበል፤

በ) የሥራ ውልን በሚኒስቴሩ ሳያፀድቅ ሠራተኛን ለሥራ ማሰማራት

ተ) በሥራ ውሉ ከተመለከተው አገር ውጭ ሠራተኛን ለሥራ መላክ፤

ቸ) በተሰጠው ፈቃድ ከተመለከተው የአገልግ ሎት ዓይነት፣ የሥራ ቦታ ወይም አገር ውጭ መሥራት፤

ኀ) ሠራተኛን በፀደቀው የሥራ ውል ከተመለከተው አሠሪ ውጭ ለሌላ አሠሪ ማስተላለፍ፤

ነ) በዚህ አዋጅ፣ በሌላ ሕግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ በውጭ አገር ሥራ ስምሪት እንዳይሰማራ የተከለከለ ሰው በኤጀንሲው ሥራ ውስጥ እንዲሳተፍ ማድረግ፤

ኘ) ሠራተኛን ለመመልመልና ለሥራ ለማሰማራት ሲባል የተሳሳተ መረጃ ወይም ሰነድ መስጠት ወይም ማስታወቂያ ማውጣት፤

አ) የፀደቀውን የሥራ ውል ሚኒስቴሩን ሳያሳውቅና ሳያፀድቅ በሌላ መተካት ወይም መቀየር፤

may submit oral or written complaint, to the Ministry or the appropriate authority when this Proclamation or any regulation or directive issued hereunder or any other relevant law has been contravened by an Agency.

2/ The complaint pursuant to sub-article (1) of this Article, if submitted orally, the officer of the Ministry or the appropriate authority shall write on hardcopy and cause the complainant to sign.

3/ The Ministry or the appropriate authority may conduct proceedings on its own initiative or based on reports received from other body on the violation of the provisions of this Proclamation.

**44. Content of Complaint**

The complaint to be submitted pursuant to Article 43 of this Proclamation shall, among other explanatory notes, include the following:

1/ name and address of the complainant;

2/ name and address of the Agency against whom a complaint was submitted;

3/ nature of the complaint, relevant facts and reasons for the complaint;

4/ time and place of the commission of the act complained;

5/ the amount of claim, if any;

6/ relief sought;

7/ other relevant supportive evidences.

**45. Complaint Hearing**

1/ The Ministry or the appropriate authority shall open a file to a complaint submitted to it pursuant to Article 43 and 44 of this Proclamation and proceed examining and hearing of the case.

2/ The Ministry or the appropriate authority shall, up on receipt of the complaint, issue summon order, together with the copy of the compliant and supporting documents, if any, directing the respondent Agency to present his statement of defense within ten working days.

3/ Where the respondent Agency fails to

ከ) ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን ሠራተኛ ወደ ሥራ ከመሰማራቱ በፊትም ሆነ በኋላ በማናቸውም ምክንያት መያዝ ወይም መከልከል፤

ኸ) የሠራተኛ የጉዞ ሰነድን ሆን ብሎ ማሳሳት ወይም መቀየር፤

ወ) ሠራተኛን በማታለል ወይም በማስገደድ ባለመብት የሆነበትን ጥቅሞች እንዲተው ማድረግ፡፡

## ፵፫. አቤቱታ ስለማቅረብ

፩/ ማንኛውም ተጎጂ ሠራተኛ ወይም የተጎጂው ሠራተኛ ተወካይ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ሌላ ተዛማጅነት ያለው ሕግ በኤጀንሲው ተጥሷል በሚል ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው
፰ሺ፰፻፹፩ ባለሥልጣን አቤቱታ በጽሁፍ ወይም በቃል ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታው የቀረበው በቃል ከሆነ የሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኦፊሰር አቤቱታውን በወረቀት ላይ በማስፈር አቤቱታ አቅራቢው እንዲፈርም ማድረግ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሌላ አካል የሚቀርብለትን በዚህ አዋጅ የተመለከተውን የሕግ ጥሰት የሚመለከት ሪፖርት መሠረት በማድረግ ጉዳዩ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ፵፬. የአቤቱታ ይዘት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፫ መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝር መግለጫዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል ፡-

፩/ የአቤቱታ አቅራቢ ስም እና አድራሻ፤

፪/ አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ ስም እና አድራሻ፤

፫/ የአቤቱታው ዓይነት፣ ፍሬ ጉዳይ እና ምክንያት፤

፬/ ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ድርጊት የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፤

፭/ በአቤቱታው የተጠየቀ ገንዘብ ካለ መጠኑ፤

፮/ የተጠየቀው መፍትሔ፤

submit his statement of defense to the complaint he received through summon pursuant to sub-article (2) of this Article ex-parte proceeding shall resume.

4/ Withdrawal of complainant by the complainant for whatever reason, shall not bar the Ministry or the appropriate authority from examining and passing decision on the complaint.

5/ The Ministry or the appropriate authority shall, within one month, render its decision on the complaint submitted to it.

## 46. Temporary Measure

The Ministry shall:

1/ not approve any contract of employment submitted by the respondent Agency, until the complaint instituted on violation of this Proclamation, regulation and directives issued hereunder has been examined and determined;

2/ suspend the respondent Agency's license until the complaint is disposed on the following grounds:

a) if the Agency against which complaint is lodged fails to appear in person or fails to present relevant document after receiving order;

b) if it is believed that the continued operation of the Agency may lead to further violation or exploitation of workers to be recruited or adversely affect relations with any country or prejudice national interest;

c) there is a prima facie evidence of a case for violation of this Proclamation, regulations or directive issued hereunder.

## 47. Administrative Measure

1/ If it is proved that an Agency has committed contraventions specified under Article 42 (2) of this Proclamation;

a) its license shall be suspended for three months, if the violation is for

፯/ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ማስረጃዎች፡፡

፵፮. **<u>አቤቱታ ስለመስማት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፫ እና ፵፬ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብ ፋይል በመክፈት አቤቱታውን የመመርመርና የመስማት ሂደት ይቀጥላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን አቤቱታ እንደደረሰው የአቤቱታውን ቅጂና ደጋፊ ሰነዶች በማያያዝ አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ መልሱን በጽሁፍ እንዲያቀርብ የመጥሪያ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በመጥሪያ ለደረሰው አቤቱታ ኤጀንሲው መልስ ካልሰጠ መልስ ሰጭ በሌለበት አቤቱታ የመስማት ሂደት ይቀጥላል፡፡

፰ሺ፰፻፹፮

፬/ አቤቱታ አቅራቢው ያቀረበውን አቤቱታ በማናቸውም ምክንያት ቢያቋርጥ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩን በመመርመር ተገቢውን ውሳኔ ከመስጠት አያግደውም፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን አቤቱታ በማጣራትና በመመርመር አቤቱታው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለጉዳዩ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፵፯. **<u>ጊዜያዊ እርምጃ ስለመውሰድ</u>**

ሚኒስቴሩ፡-

፩/ ይህን አዋጅ፣ አዋጁን መሠረት አድርጎ የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በመጣሱ ምክንያት የቀረበበትን አቤቱታ አጣርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተጠሪው ኤጀንሲ በኩል የሚቀርብን የሥራ ውል አያፀድቅም፤

፪/ በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በሚከተሉት ምክንያቶች የኤጀንሲውን ፈቃድ አግዶ ያቆያል፡-

ሀ) አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ በአካል እንዲቀርብ ወይም አስፈላጊውን ሰነድ

the first time;

b) its license shall be suspended for six months, if the violation is for the second time;

c) its license shall be suspended for twelve months, if the violation is for a third time.

2/ If the Agency contravenes Article 42 (2) of this Proclamation for the fourth time or if it has committed any of the contraventions specified under Article 42 (3) of this Proclamation, its license shall be revoked..

3/ Commission of any of the contraventions from paragraph (a) to (s) excluding paragraph (c) of Article 42 (3) of this Proclamation shall entail criminal liability according to the circumstance as per appropriate criminal law besides to Administrative measure.

48. **<u>Legal consequences of license suspension or revocation</u>**

1/ An Agency whose license has been suspended or revoked shall cease to engage in any overseas employment exchange service.

2/ An Agency whose license has been revoked shall, within five working days, return the license to the Ministry.

3/ Whenever the Ministry suspends or revokes the license of an Agency for any reason; this fact shall be notified to appropriate organs and to the public at large through convenient means.

4/ Whenever the appropriate authority suspends the license of an Agency for any reason; this fact shall be notified to appropriate organs and to the public at large through convenient means.

5/ Suspension or revocation of license does not relieve an Agency from responding to lawful requests of the workers it sent overseas.

49. **<u>Content of Decision</u>**

The decision of the Ministry or the appropriate authority rendered in accordance with Article 45 (5) of this Proclamation shall be written in short and precise manner and contain the following:

https://ethiodata.et/

እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ደርሶት ይህንኑ ካልፈፀመ፤

ለ) ኤጀንሲው ሥራውን ቢቀጥል በሚመለ ምላቸው ሠራተኞች ላይ የከፋ የመብት ጥሰት ወይም ብዝበዛ የሚያስከትል ወይም ከማንኛውም አገር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚጎዳ ወይም የአገርን ጥቅም የሚፃረር ድርጊት ለመኖሩ አሳማኝ ከሆነ፤

ሐ) ይህን አዋጅ፣ አዋጁን መሠረት አድርጎ የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በተጠሪው ኤጀንሲ ስለመጣሱ የሚያስረዳ ማስረጃ ከቀረበ፡፡

፶፯. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ (፪) የተመለከተው ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፣

ሀ) ድርጊቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ለሦስት ወር፣

ለ) ድርጊቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ለስድስት ወር፣

ሐ) ድርጊቱ ለሦስተኛ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ለአሥራ ሁለት ወር፣



..ቃዱ ይታገዳል፡፡

፪/ ማንኛውም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ (፪) የተጠቀሰውን ጥፋት ለአራተኛ ጊዜ ወይም በአንቀጽ ፵፪ (፫) የተመለከተውን ማንኛውንም ጥፋት መፈፀሙ ሲረጋገጥ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፪ (፫) ከፊደል ተራ (ሐ) በስተቀር ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ወ) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን መፈጸም ከአስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ እንደ ሁኔታው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

፶፰. <u>የፈቃድ መታገድ ወይም መሰረዝ የሚያስከትለው ውጤት</u>

፩/ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ኤጀንሲ ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት ተግባሩን ያቆማል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃዱ የተሰረዘበት ኤጀንሲ እርምጃው በተወሰደ በአምስት የሥራ

1/ material facts;

2/ issue framed;

3/ laws, regulations or directives relevant to the issue;

4/ reasoning and conclusion;

5/ crux of the decisions;

**50. <u>Execution Order</u>**

1/ The Ministry or the appropriate authority shall issue an execution order to the respondent Agency to execute its decision rendered in accordance with Article 45 (5) of this Proclamation.

2/ The respondent Agency shall, within 15 days, execute the order of the Ministry or the appropriate authority issued pursuant to sub-article (1) of this Proclamation.

**51. <u>Priority of Execution</u>**

When an Agency held liable by the decision of Ministry or the appropriate authority or the organ empowered to entertain labor disputes upon contravening the recruitment process prescribed under this Proclamation, but fails to execute the decision, the following priority of execution shall be applied.

1/ over the Agency's blocked account allocated for the overseas workers' security bond;

2/ over the Agency's movable property if the Agency is sole proprietor or over the movable property of the business if the Agency is a business organization;

3/ over the Agency's immovable property if the Agency is sole proprietor or over the immovable property of the business if the Agency is a business organization.

**<u>SECTION TWO</u>**

**<u>VIOLATIONS BY AN EMPLOYER, AN AGENCY'S REPRESENTATIVE AND WORKERS AND THE CORRESPONDING MEASURES</u>**

**52. <u>Power to Decide Administrative Matters</u>**

The Ministry or the appropriate authority shall have the power to hear and decide administrative matters that emanate from the violation of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder by the

https://ethiodata.et/

ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለሚኒስቴሩ ይመልሳል፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ በማናቸውም ምክንያት የኤጀንሲን ፈቃድ ሲሰርዝ ወይም ሲያግድ ይህንኑ ለሚመለከታቸው አካላትና ለሕብረተሰቡ አመቺ በሆነ መንገድ ያሳውቃል፡፡

፬/ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በማናቸውም ምክንያት የኤጀንሲን ፈቃድ ሲያግድ ይህንኑ ለሚመለከታቸው አካላትና ለሕብረተሰቡ አመቺ በሆነ መንገድ ያሳውቃል፡፡

፭/ ፈቃድ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ኤጀንሲ የላካቸው ሠራተኞች ከሚያነሱት የመብት ጥያቄ ነፃ አያደርገውም፡፡

**፶፱. <u>የውሳኔው ይዘት</u>**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፰(፭) መሠረት በጽሁፍ የሚሰጠው ውሳኔ ግልፅና አጭር ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

፩/ የጉዳዩን ፍሬ ነገር፤

፪/ የጉዳዩን ጭብጥ፤

፫/ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ፤

፬/ ምክንያቶቹ እና ማጠቃለያ፤

፰ሺ፰፻፹

፭/ የተሰጠ ውሳኔ፡፡

**፷. <u>የአፈፃፀም ትዕዛዝ ስለመስጠት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፵፰(፭) መሠረት የሰጠውን ውሳኔ ኤጀንሲው እንዲፈጽም የጽሁፍ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሰጠውን ትዕዛዝ አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የመፈፀም ግዴታ አለበት፣

**፷፩. <u>የውሳኔ አፈፃፀም ቅደም ተከተል</u>**

በዚህ አዋጅ መሠረት የሠራተኛ ምልመላ ሥርዓት ጥሰት በመፈፀሙ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወይም የሥራ ክርክር ለማየት ሥልጣን በተሰጠው አካል የተወሰነን ውሳኔ በሚመለከት የተሰጠን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ኤጀንሲው ካልፈፀመ ውሳኔው በሚከተለው ቅደም ተከተል

employer, representative Agency or a worker.

**53. <u>Violations Committed by Employer and Representative of Agency</u>**

The following violations shall suffice to impose appropriate measure, against employer or representative of an Agency:

1/ failure to discharge its obligation as agreed in the contract of employment;

2/ failure to discharge its obligation as per the delegation;

3/ withholding or denying access to the worker's legal travel documents for whatever reasons;

4/ withholding, without good cause, the workers wage or his remittances;

5/ negligently causing serious injury, health problem or death on the worker;

6/ committing an act that violates worker's human dignity and moral;

7/ commission of sexual harassment on the worker

8/ contravention of the provision of this Proclamation, regulations or directives issued hereunder.

**54. <u>Complaint Against an Employer or a Representative Agency and the Decision Making</u>**

1/ A victim worker or any person may submit oral or written complaint to the Ministry or the appropriate authority alleging the commission of violation by employer or a representative of Agency.

2/ The complaint pursuant to sub-article (1) of this Article, if submitted orally, the officer of the Ministry or the appropriate authority shall write on hardcopy and cause the complainant to sign.

3/ The Ministry or the appropriate authority may conduct proceedings on its own initiative or based on reports received from other body on the violation of the provisions of this Proclamation.

4/ An employer or a representative Agency against whom a complaint has been lodged may temporarily be suspended from employing worker from Ethiopia or participating in overseas employment

ተፈፃሚ ይሆናል ፦

፩/ ኤጀንሲው ለሠራተኞች ዋስትና ማስከበሪያ በዝግ ሂሳብ በባንክ ባስቀመጠው ገንዘብ፤

፪/ ኤጀንሲው የግል ድርጅት ከሆነ በሚንቀሳቀስ የግል ንብረት ላይ ወይም ኤጀንሲው የንግድ ማኅበር ከሆነ በሚንቀሳቀስ የማኅበሩ ንብረት ላይ፤

፫/ ኤጀንሲው የግል ድርጅት ከሆነ በማይንቀሳቀስ የግል ንብረት ላይ ወይም ኤጀንሲው የንግድ ማኅበር ከሆነ በማይንቀሳቀስ የማኅበሩ ንብረት ላይ፡፡

**<u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>**

**<u>በአሠሪ፣ በኤጀንሲ ወኪል ወይም በሠራተኛ የሚፈፀም ጥፋትና የሚወሰድ ዕርምጃ</u>**

**፶፪. <u>አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመወሰን ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በአሠሪ፣ የኤጀንሲ ወኪል ወይም ሠራተኛ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብና መመሪያ በመጣሱ ምክንያት የሚነሱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመስማትና የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

**፶፫. <u>በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ ወኪል ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>**



በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ ወኪል ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቁ ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው ፦

፩/ በገባው የሥራ ውል መሠረት ግዴታውን አለመወጣት፤

፪/ በውክልናው መሠረት ግዴታውን አለመወጣት፤

፫/ የሠራተኛን ሕጋዊ የጉዞ ሰነዶች በማናቸውም ምክንያት መያዝ ወይም እንዳያገኝ መከልከል፤

፬/ የሠራተኛን ደመወዝ ወይም ሠራተኛው ወደ አገር የሚልከውን ገንዘብ ያለበቂ ምክንያት መያዝ፤

፭/ በቸልተኝነት ሠራተኛው ላይ ከባድ ጉዳት፣ ህመም ወይም የሞት አደጋ ማድረስ፤

፮/ የሠራተኛውን ሰብዓዊ ክብርና ሞራል የሚነካ

exchange service until such time the complaint is disposed of.

5/ The Ministry or the appropriate authority shall, within one month, render decision on the complaint submitted before it.

**55. <u>Content of the Complaint</u>**

Any complaint submitted pursuant to Article 54 (1) and (2) of this Proclamation shall contain the following information:

1/ the name and address of the complainant;

2/ the name and address of the employer or a representative of Agency against whom complaint is lodged;

3/ the nature of the violation committed;

4/ the time and place of the violation committed;

5/ other supportive evidences.

**56. <u>Legal Consequence of the Decision</u>**

Where the Ministry or the appropriate authority ascertains that the employer or a representative of Agency has committed the contravention complained of:

1/ the employer shall be prohibited from employing worker from Ethiopia;

2/ the representative of the Agency shall be prohibited from participating in the Ethiopian overseas employment activity;

3/ the employer or the representative of the Agency shall be liable to pay reasonable compensation for the contravention it committed pursuant to Article 53 of this Proclamation.

**57. <u>Contraventions by a worker</u>**

The following violations shall suffice to impose appropriate measure against worker:

1/ failure to discharge his obligation he as agreed in the contract of employment;

2/ commission of crimes punishable in Ethiopia or in the country of destination;

3/ failure to respect the religion, custom or customary practice of the country of destination;

4/ unwillingness to be deployed, without good cause, after the contract of

ድርጊት መፈጸም፤

፯/ በሠራተኛው ላይ ጸታዊ ጥቃት መፈጸም፤

፰/ ይህን አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ወይም መመሪያን መጣስ፡፡

**፶፬. <u>በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ ወኪል ላይ የአቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ</u>**

፩/ ተጎጂ ሠራተኛ ወይም ማንኛውም ሰው በአሠሪው ወይም በኤጀንሲ ወኪል ጥፋት ተፈጽሟል በሚል አቤቱታ በጽሁፍ ወይም በቃል ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማቅረብ ይችላል፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አቤቱታው የቀረበው በቃል ከሆነ የሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ኦፊሰር አቤቱታውን በወረቀት ላይ በማስፈር አቤቱታ አቅራቢው እንዲፈርም ማድረግ አለበት፡፡

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሌላ አካል የሚቀርብለትን በዚህ አዋጅ የተመለከተውን የሕግ ጥሰት የሚመለከት ሪፖርት መሠረት በማድረግ ጉዳዩ እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ አቤቱታ የቀረበበት አሠሪ ወይም የኤጀንሲ ወኪል ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከኢትዮጵያ ሠራተኛ እንዳይቀጥር ወይም በውጭ አገር ሥራ ስምሪት እንዳይሳተፍ ለጊዜው በሚኒስቴሩ ሊታገድ ይችላል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን አቤቱታ በማጣራት እና በመመርመር አቤቱታው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፲ሺ፲፻፹

**፶፭. <u>የአቤቱታ ይዘት</u>**

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፶፬ (፩) እና (፪) መሠረት የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል ፦

፩/ የአቤቱታ አቅራቢው ስም እና አድራሻ፤

፪/ አቤቱታ የቀረበበት አሠሪ ወይም የኤጀንሲ

employment has been approved by the Ministry;

5/ an unauthorized use of employers' or colleagues money or property;

6/ production of falsified evidence for overseas employment;

7/ terminating contract of employment without good cause.

**58. <u>Administrative Measures</u>**

Without prejudice to the liability of the worker in accordance with other relevant laws for the contravention of Article 57 of this Proclamation, the following administrative measures shall apply:

1/ if the contravention is committed for the first time, the worker shall be suspended from overseas employment for six months;

2/ if the contravention is committed for the second time, the worker shall be suspended from overseas employment for one year;

3/ if the contravention is committed for the third time, the worker shall be disqualified from overseas employment;

**59. <u>Right to Lodge Pleading before Court of Law</u>**

1/ A party aggrieved by the decision of the Ministry or the appropriate authority that emanate from the violation of this proclamation , regulations and directives issued here under may, within fifteen days, lodge his pleading to the Federal High Court or a regional court having jurisdiction,.

2/ The decision given by court of law pursuant to sub-article (1) of this Article shall be final.

**<u>PART SIX</u>**

**<u>WELFARE SERVICE</u>**

**<u>SECTION ONE</u>**

**<u>FINANCIAL GUARANTEE AND INSURANE</u>**

**60. <u>Financial Guarantee</u>**

1/ Any Agency shall deposit USD 100,000 or its equivalent in Birr in a blocked bank account for purposes of guaranteeing the protection of the rights

https://ethiodata.et/

ወኪል ስም እና አድራሻ፤

፫/ የተፈጸመ ጥፋት ዓይነት፤

፬/ ጥፋቱ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፤

፭/ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች፡፡

## ፶፮. <u>ውሳኔው የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት</u>

አቤቱታ የቀረበበት አሠሪ ወይም የኤጀንሲ ወኪል ጥፋት መፈጸሙ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ውሳኔ ከተረጋገጠ ፦

፩/ አሰሪው ከኢትዮጵያ ውስጥ ሠራተኛን ለመቅጠር አይፈቀድለትም፤

፪/ የኤጀንሲው ወኪል በኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ስምሪት ተግባር ሊሳተፍ አይችልም፤

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ መሠረት በተፈፀመው ጥፋት ምክንያት በሠራተኛው ላይ ለደረሰ ጉዳት አሠሪው ወይም የኤጀንሲው ወኪል ተመጣጣኝ ካሣ ይከፍላል፡፡

## ፶፯. <u>በሠራተኛ ስለሚፈፀሙ የጥፋት ዓይነቶች</u>

የሚከተሉት ጥፋቶች በሠራተኛ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቁ ናቸው ፦

፩/ በገባው የሥራ ውል መሠረት ግዴታውን አለመወጣት፤

፪/ በኢትዮጵያ ወይም በተቀባይ አገር ባሉ ሕጎች በወንጀል የሚያስቀጣ ድርጊት መፈፀም፤

፫/ የተቀባይ አገር እምነት፣ ባህል እና ልማድን የሚፃረር ድርጊት መፈፀም፤

፬/ አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የሥራ ውሉ ከፀደቀ በኋላ ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ለመሰማራት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት፤

፭/ የአሠሪን ወይም አብሮ የሚሰራ ሠራተኛን ገንዘብ ወይም ንብረት ያለአግባብ መጠቀም፤

፳ሺ፳፻፺

፮/ ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ የተሳሳተ መረጃ ማቅረብ፤

፯/ ያለበቂ ምክንያት የሥራ ውል ማቋረጥ፡፡

## ፶፰. <u>ስለሚወሰድ ዕርምጃ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፯ የተመለከተውን ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሠራተኛ አግባብ ባለው ሕግ

and safety of deployed workers.

2/ The amount of money deposited in blocked bank account pursuant to sub-article (1) of this Article shall not be released unless permission is obtained from the Ministry.

3/ Where the Agency fails to execute the duty imposed on it pursuant to paragraph (a) and (b) of Article 69(1) of this Proclamation, the Ministry is empowered to withdraw the required amount from the deposited guarantee money and use for the intended purpose.

4/ Where the deposited amount has been used pursuant to Article 51 (1) of this Proclamation and sub-article (3) of this Article, the Agency shall replenish the fund within 10 working days.

5/ Whenever the Agency ceases operation in what so ever condition, its financial guarantee shall be released by the Ministry, when there is no claim against the Agency before any competent organ and after six months from the termination of the employment contracts of all workers who were deployed overseas by the Agency.

## 61. <u>Foreign Employers' Guarantee Fund</u>

1/ A Foreign Employers' Guarantee Fund shall be established pursuant to this Proclamation for all workers hired by a foreign Governmental Organizations through the Ministry or a foreign employer who has been allowed for direct employment, for the purpose of covering claims of workers that may arise from breach of contract of employment.

2/ The foreign employer specified under sub-article (1) of this Article shall, for each worker it recruits, allocate USD 50 to the Foreigner Employers' Guarantee Fund established hereunder.

3/ The Fund established under sub-article (1) of this Article shall be administered by the Ministry.

4/ The Fund shall only be utilized:

a) mainly for settling claims pursuant to sub-article (1) of this Article;

ተጠያቂ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ፦

፩/ ጥፋቱን የፈፀመው ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ዕድል ለስድስት ወር ጊዜ ይታገዳል፤

፪/ ጥፋቱን የፈፀመው ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ዕድል ለአንድ ዓመት ጊዜ ይታገዳል፤

፫/ ጥፋቱን የፈፀመው ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ለውጭ አገር ሥራ ስምሪት ብቁ አይሆንም፡፡

## ፶፱. ለፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በሚፈፀመው ጥፋት ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በደረሰው በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በክልል ሥልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በፍርድ ቤት ታይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ስለዋስትና ገንዘብና ኢንሹራንስ

## ፷. ስለዋስትና ገንዘብ

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ ለሠራተኛው መብት እና ደህንነት ዋስትና ማስከበሪያ የሚውል $100,000(አንድ መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) ወይም ተመጣጣኙን የኢትዮጵያ ብር በዝግ ሂሳብ በባንክ ማስቀመጥ አለበት፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ካልፈቀደ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በዝግ ሂሳብ የተቀመጠውን ገንዘብ ጉዳዩ የሚመለከተው ባንክ በማናቸውም ሁኔታ መልቀቅ አይችልም፡፡



፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰፱ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ኤጀንሲው ካልፈጸመ ሚኒስቴሩ ተቀማጭ ከሆነው የዋስትና ገንዘብ

b) for purchasing treasury bonds and for profitable and convenient investments as determined by the directive of the Ministry of Finance and Economic Cooperation.

5/ The Guarantee Fund shall not be subject to attachment or set-off any payment of debit.

## 62. Insurance Coverage

1/ The employer shall, from the domestic insurance market, buy life and disability insurance of the worker deployed overseas. The Ministry may issue a directive prescribing the details.

2/ An Agency or the worker shall present to the Ministry the insurance policy document accompanied with contract of employment.

## SECTION TWO

## ASSISTANCE PROVIDED TO WORKERS

## 63. Responsibility

1/ The Ministry and, as appropriate, the Ministry of Foreign Affairs shall have the responsibility to ensure that the rights, safety and dignity of worker deployed in overseas employment are respected.

2/ Any Agency shall have duty to cause the employer to respect obligations enshrine in the contract of employment with respect to a worker he has deployed overseas.

## 64. Provision of Support

1/ The Ministry or the appropriate authority may entertain request for support claimed by the worker or a person who has concern for the worker in connection with issues of overseas employment.

2/ When support is requested pursuant to sub-article (1) of this Article, the Ministry or the appropriate authority shall order the Agency to act up on support sought or problem brought to its attention and to submit report on the status or condition of the worker.

3/ Where the Agency or the employer fails to

https://ethiodata.et/

ላይ ወጪ በማድረግ ለተፈለገው ዓላማ ያውላል፡፡

፬/ ተቀማጭ የሆነው የዋስትና ገንዘብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፩(፩) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በጥቅም ላይ ከዋለ ኤጀንሲው ተቀናሽ የሆነውን የዋስትና ገንዘብ መጠን በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ መልሶ መተካት ይኖርበታል፡፡

፭/ ኤጀንሲው በማናቸውም ሁኔታ ሥራውን ሲያቆም ሚኒስቴሩ የዋስትናውን ገንዘብ የሚለቀው ከሠራተኛ መብትና ጥቅም ጋር የተያያዘ ጥያቄ ሥልጣን በተሰጠው አካል በመታየት ላይ ካልሆነ እና በኤጀንሲው አማካይነት ለሥራ ወደ ውጭ አገር የተላኩ ሠራተኞች በሙሉ የሥራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ፮ ወር በኋላ ነው፡፡

## ፷፩. የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ

፩/ በሚኒስቴሩ አማካኝነት ሠራተኛን የሚቀጥር ማንኛውም የውጭ አገር መንግሥታዊ ድርጅትም ሆነ ቀጥታ ቅጥር የተፈቀደለት ማንኛውም የውጭ አገር አሠሪ የሚቀጥራቸው ሠራተኞች በሥራ ውል መጣስ ምክንያት የሚያነሱትን የገንዘብ ክፍያ ጥያቄዎች መሸፈን እንዲቻል የውጭ አሠሪዎች የዋስትና ፈንድ በዚህ አዋጅ መሠረት ይቋቋማል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የውጭ አገር አሠሪ ለቀጠረው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ ፶ የአሜሪካን ዶላር በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ለተቋቋመው የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ መዋጮ ያደርጋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተቋቋመውን የውጭ አሠሪዎች ዋስትና ፈንድ የሚያስተዳድረው ሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬/ የዋስትና ፈንዱ ጥቅም ላይ የሚውለው ፡-

ሀ) በዋነኛነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት የሠራተኞችን የገንዘብ ክፍያ ጥያቄ ለመሸፈን፣ እና

ለ) ለትሬዠሪ ቦንድ መግዣና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰኑ ሌሎች አትራፊና

act for support requested by the worker or a person who has concern for the worker, the Ministry or the appropriate authority may take the necessary administrative measure in accordance with this Proclamation.

4/ The Ministry or the appropriate authority shall, in cooperation with concerned bodies, facilitate reintegration supports for Ethiopian overseas workers deployed and return in accordance with this Proclamation; the details of which shall be specified in the directive.

5/ The Ministry or the appropriate authority shall provide legal assistance to workers victimized in connection with overseas employment.

## 65. Registration of worker on leave or vacation

Any worker coming to homeland being on leave or vacation and returning back to same employer shall be registered by the Ministry upon presentation of the following documents:

1/ valid passport;

2/ visa and work permit valid for the country of destination;

3/ other evidences to be requested by the Ministry.

## SECTION THREE
## CONCILIATION AND REPATRIATION OF WORKERS

## 66. Conciliation

The Ministry or the appropriate authority may receive and conciliate any complaint submitted to it by a worker, an Agency or employer relating to overseas employment.

## 67. Conciliation Proceedings

1/ The Ministry or the appropriate authority shall, upon receipt of a complaint, notify within three working days to the respondent and strive to bring concerned parties together to discuss the possibility of arriving at an amicable settlement within fifteen working days.

2/ The issues, on which amicable settlement is reached, shall be binding and enforceable.

አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች፣ ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ የዋስትና ፈንዱ በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት መያዣ ወይም ማቻቻያ ሊሆን አይችልም፡፡

**፸፪. ስለኢንሹራንስ ሽፋን**

፩/ ማንኛውም ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለሚሄድ ሠራተኛ አሠሪው የሕይወትና የአካል ጉዳት ካሳ ኢንሹራንስ ሽፋን በአገር ውስጥ የመግባት ግዴታ አለበት፤ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ ኤጀንሲ ወይም ሠራተኛ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሰነዱን ከሥራ ዉል ጋር አያይዞ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ለሠራተኞች ስለሚደረግ ድጋፍ**

**፸፫. ኃላፊነት**

፩/ ሚኒስቴሩ እና እንደ አግባቡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ አገር ለሥራ የተሰማራ ሠራተኛ መብት፣ ደህንነትና ክብር መጠበቁን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ ማንኛውም ኤጀንሲ ለሥራ የላከውን ሠራተኛ አስመልክቶ አሠሪው በሥራ ውሉ መሠረት ያሉበትን ግዴታዎች እንዲያከብር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

**፸፬. ስለድጋፍ አሰጣጥ**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ወይም ስለሠራተኛው ያገባኛል ከሚል ሰው የሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ በመቀበል ሊያስተናግድ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ስለቀረበው የድጋፍ ጥያቄ ወይም ሠራተኛው ስለገጠመው ችግር ኤጀንሲው ተገቢውን መፍትሄ በመስጠት ሠራተኛው ስላለበት ሁኔታ ሪፖርት እንዲያቀርብ ያዛል፡፡

፫/ በሠራተኛ ወይም ስለሠራተኛው ያገባኛል ከሚል ሰው ለሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ

3/ Where efforts for amicable settlement fail, the complainant may submit his case to adjudication office of the Ministry or appropriate authority, as appropriate.

**68. Administrative Measures**

Where the Agency against whom complaint was lodged fails, without good cause,

1/ to appear on the date specified for conciliation, or

2/ to abide by the terms of the approved settlement,

the Ministry shall not approve any contract of employment submitted by the Agency, until it complies thereto.

**69. Repatriation of Workers**

1/ Any Agency shall have the following obligations:

a) transporting back the worker and his personal belongings by covering air transport fee upon termination of contract of employment;

b) where the workers sustains serious bodily injury or dies, unless there is valid reason for delay, shall repatriate his body and personal effects accompanied with legal medical certificate witnessing his injury or death within 15 days and shall cover all expenses of air transport associated with the repatriation;

c) Cover medical expenses to a worker who has been repatriated due to serious bodily injury.

2/ Where the worker terminates his contract of employment without good cause, the Agency may reclaim its expenses after repatriating the worker.

**PART SEVEN**

**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**70. Determining Number of Agencies Work with one Representative and an Agency with Representatives**

The Ministry shall determine by directive the number of Ethiopian Agencies to be

የሚመለከተው ኤጀንሲ ወይም አሠሪ ተገቢውን መፍትሄ ካልሰጠ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

፬/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሥራ ውጭ አገር ሄደው ወደ አገራቸው ለሚመለሱ ዜጎች የማቋቋሚያ ድጋፍ ያመቻቻል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ ተጎጂ ለሆነ ሠራተኛ ነፃ የሕግ ምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## ፸፭. በፈቃድ ወይም ለዕረፍት ወደ አገር የሚመጣ ሠራተኛን ስለመመዝገብ

በፈቃድ ወይም ለዕረፍት ወደ አገር የሚመጣና ይሰራበት ወደ ነበረው አሠሪ የሚመለስ ማንኛውም ሠራተኛ የሚከተሉትን ሰነዶች ለሚኒስቴሩ በማቅረብ መመዝገብ ይኖርበታል ፦

፩/ የፀና ፓስፖርት፤

፪/ ወደ ተቀባይ አገር መመለሻ ቪዛና የሥራ ፈቃድ፤

፫/ በሚኒስቴሩ የሚጠየቁ ሌሎች ማስረጃዎች፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለማስማማት እና ሠራተኛን ወደ አገር ስለመመለስ

## ፸፮. ስለማስማማት

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለሥልጣን ከውጭ አገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ በሠራተኛ ፣በኤጀንሲ ወይም በአሠሪ ላይ የሚቀርብ አቤቱታን ተቀብሎ ሊያስማማ ይችላል፡፡

## ፸፯. ስለማስማማት ሂደት

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለሥልጣን አቤቱታን በተቀበለ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታ ለቀረበበት አካል በማሳወቅ ሁለቱ ወገኖች ቀርበው ጉዳዩን በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ በስምምነት እንዲጨርሱ ጥረት ያደርጋል፡፡

፪/ ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች በሁለቱ

represented by a single licensed representative in the country of destination and the number of representatives in the country of destination with whom an Ethiopian Agency works.

## 71. Labor Dispute Resolution

Any dispute arising between the worker and the employer or an Agency in connection with rights and claims shall be resolved before a Labor Bench established pursuant to Labor Proclamation.

## 72. Burden of Proof

Whenever a worker deployed for overseas employment institutes a court case pertaining to work conditions and if the employer or the Agency objects the proceeding, the burden of proof lies on the Agency or the employer to show that the action does not have a legally valid ground.

## 73. Period of Limitation

Any administrative complaint against an employer, Agency, representative of Agency or a worker for violations of this Proclamation shall be barred by limitation unless submitted to the Ministry within three years from the date of commission of the wrong or from the time the commission of the wrong was known.

## 74. Prohibition

1/ For any person it is prohibited to receive service charge from a worker for overseas employment exchange service.

2/ The Ministry may prohibit the overseas movement of citizens for employment, whenever the country of destination is believed to be a war-zone, affected by natural calamities or contagious diseases which endanger the safety of citizens.

## 75. Power to issue Regulation and Directives

1/ The Council of Ministers may issue regulations for the proper implement ation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives for the proper implementation of this Proclamation and the regulation to be

ወገኖች ላይ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፫/ የማስማማቱ ጥረት ካልተሳካ አቤቱታአቅራቢው ጉዳዩን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን የአቤቱታ መወሰኛ ሥራ ክፍል

ማቅረብ ይችላል፡፡



## ፸፰. አስተዳደራዊ እርምጃ

አቤቱታ የቀረበበት ኤጀንሲ በቂ ባልሆነ ምክንያት፦

፩/ ለማስማማት በተያዘው ቀጠሮ ቀን ያልቀረበ እንደሆነ፣ ወይም

፪/ የተደረሰበትን ስምምነት ተግባራዊ ያላደረገ እንደሆነ፣

ይህንኑ እስኪፈጽም ድረስ በኤጀንሲው በኩል የሚቀርብ የሥራ ውልን ሚኒስቴሩ አያፀድቅም፡፡

## ፸፱. ሠራተኛን ወደ አገር ስለመመለስ

፩/ ማንኛውም ኤጀንሲ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል ፦

ሀ) የሥራ ውል እንደተቋረጠ የአየር ትራንስፖ ርት ወጪ በመሸፈን ሠራተኛውንና የግል ንብረቶቹን ወደ አገሩ የመመለስ፤

ለ) ሠራተኛው ከባድ የአካል ጉዳት ሲደርስበት ወይም ሲሞት ጉዳት የደረሰበትን ሠራተኛ ወይም አስከሬን የሚቆይበት በቂ ምክንያት ከሌለ በስተቀር ከግል ንብረቶቹ ጋር የአየር ትራንስፖርት ወጪ በመሸፈን ሠራተኛው ስለደረሰበት ጉዳት ወይም ሞት ከሚገልጽ ሕጋዊ የህክምና ማስረጃ ጋር በማያያዝ በ፲፫ ቀናት ውስጥ ወደ አገሩ የመመለስ እና ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ወጪዎችን የመሸፈን፤

ሐ) የሥራ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ ወደአገር ሲመለስ አስፈላጊ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ሕክምና እንዲያገኝ የማድረግ፡፡

፪/ ሠራተኛው የሥራ ውሉን ያለበቂ ምክንያት ካቋረጠ ኤጀንሲው ሠራተኛውን ወደአገሩ በመመለስ ያወጣውን ወጪ ሊጠይቅ

issued pursuant to sub-article (1) of this Proclamation.

## 76. Duty to Cooperate

Any person shall have duty to cooperate for the proper implementation of this Proclamation.

## 77. Repeal and Inapplicable Laws

1/ Employment Exchange Service Proclamation No. 632/2009 is hereby repealed.

2/ No law, regulations, directives or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable in respect of matters provided for in this Proclamation.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, regulations and directives issued pursuant to Proclamation No.632/2009 shall, in so far as they are not inconsistent with this Proclamation, remain in force until replaced by regulations and directives to be issued pursuant to this Proclamation.

## 78. Transitory Provisions

1/ Any dispute pertaining to overseas employment pending before any competent organ to settle labour disputes prior to the coming into force of this Proclamation shall be settled in accordance with the law and procedure which were in force before the coming into force of this Proclamation.

2/ Any Agency licensed for overseas employment service by virtue of the Proclamation No.632/2009, if wishes to resume the service, shall issue a new license within three months from the effective date of this Proclamation. Failure to issues new license within the time-limit shall make the former license null and void.

3/ Notwithstanding the provision of sub-article (2) of this Article, revocation of license may not relieve an Agency from

ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፹. አንድ ወኪል ከምን ያህል ኤጀንሲዎች እና አንድ ኤጀንሲ ከምን ያህል ወኪሎች ጋር መሥራት እንደሚችል ስለመወሰን**

በተቀባይ አገር ሥራና ሠራተኛ ለማገናኘት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ወኪል በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ከምን ያህል ኤጀንሲዎች ጋር ወኪል ሆኖ መሥራት እንደሚችል እንዲሁም ፈቃድ ያለው ኤጀንሲ በተቀባይ አገር ፈቃድ ካለው

ምን ያህል ወኪል ጋር መሥራት እንደሚችል ሚኒስቴሩ በመመሪያ ይወስናል፡፡

**፹፩. ስለ ሥራ ክርክር አፈታት**

በሠራተኛ እና በአሠሪ ወይም በኤጀንሲ መካከል ካለው የሥራ ግንኙነት በመነጨ የሚነሳ ማናቸውም የመብትና የጥቅም ክርክር ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት በተቋቋመ የሥራ ክርክር ችሎት ይታያል፡፡

**፹፪. የማስረዳት ግዴታ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ሠራተኛ በሥራ ሁኔታዎች ላይ የሚያቀርበውን ክስ ወይም አቤቱታ ኤጀንሲው ወይም አሠሪው ከተቃወመ ክሱ ወይም አቤቱታው ሊደገፍ እንደማይገባ የማስረዳት ግዴታ የሚወድቀው በኤጀንሲው ወይም በአሠሪው ላይ ይሆናል፡፡

**፹፫. ስለ ይርጋ**

በዚህ አዋጅ መሠረት በአሠሪ፣ በኤጀንሲ፣ በኤጀንሲ ወኪል ወይም በሠራተኛ በሚፈፀም ጥፋት ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም አስተዳደራዊ አቤቱታ ጥፋቱ ከተፈፀመበት ወይም ጥፋቱ መፈፀሙ ከታወቀበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ዓመት ድረስ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው ባለሥልጣን ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**፹፬. ክልከላ**

፩/ ማንኛውም ሰው ሠራተኛን ገንዘብ በማስከፈል የውጭ አገር ሥራና ሠራተኛ የማገናኘት ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የሚሄዱ ዜጎች የሚሄዱበት አገር በጦርነት ቀጠና፣ በተፈጥሮ አደጋ ወይም በበሽታና በመሳሰሉት

rightful claims arising from workers' it deployed.

4/ Notwithstanding the provisions of Article 77 (1) of this Proclamation, the Proclamation No.632/2009 shall apply on local employment exchange service and on new applicants for local employment exchange service until a new law pertaining to it is issued.

**79. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa on the 19th day of February, 2015**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://ethiodata.et/

ምክንያቶች ለዜጎች ደህንነት አስጊ መሆኑን ካመነ ለሥራ ተቀጥረው እንዳይሄዱ ሊከለክል ይችላል፡፡

**፸፩. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልገውን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለዚህ አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፰ሺ፰፻፺፰

**፸፪. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፸፫. የተሻሩና ተፈፃሚ የማይሆኑ ሕጎች**

፩/ ስለ ሥራና ሠራተኛ ማገናኘት አገልግሎት የወጣ አዋጅ ቁጥር ፯፻፴፪/፪ሺ፩ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ በአዋጅ ቁጥር ፯፻፴፪/፪ሺ፩ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

**፸፬. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

፩/ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የተላከን ሠራተኛ በሚመለከት ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት በማናቸውም የሥራ ክርክር ሰሚ አካል ዘንድ በመታየት ላይ ያለ የሥራ ክርክር በተጀመረበት ሕግና ሥርዓት መሠረት ፍፃሜ ያገኛል፡፡

፪/ በአዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ መሠረት ሠራተኛን በውጭ አገር ለሥራ ለማሰማራት ፈቃድ ተሰጥቶት የነበረ ማንኛውም ኤጀንሲ ሥራውን መቀጠል የሚፈልግ ከሆነ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ አዲስ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ አዲስ ፈቃድ ሳያወጣ ቢቀር ቀድሞ ተሰጥቶት የነበረው ፈቃድ ዋጋ አልባ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተደነገገው ቢኖርም ፈቃዱ የተሰረዘበት ኤጀንሲ ለሥራ ወደ ውጭ አገር የላካቸው ሠራተኞች ከሚያነሱት ማናቸውም የመብት ጥያቄ ነፃ አያደርገውም፡፡

፰ሺ፰፻፺፯

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፸፯ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የፀና ፈቃድ ላለው ማንኛውም የአገር ውስጥ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ እና በሀገር ውስጥ አዲስ ፈቃድ ለሚጠይቅ ሰው አግባብ ያለው ሌላ ሕግ እስኪወጣ ድረስ አዋጅ ቁጥር ፮፻፴፪/፪ሺ፩ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፸፱. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

.

https://ethiodata.et/